


የግሸን የመጌር መስቀል

# ንሥሐ



ጥንታዊቷ የግፍት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ጥር ፩፻፵፬

የመስከረምና የጥቅምት ፲፱፻፹፫ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጕሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም/አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
• የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

## ማውጫ ፡

## ርእስት

ገጽ

ደብዳቤዎች ........ ፩
(ርእሰ አንቀጽ) እጅግ በጣም ተጨንቄያለሁ ። ........ ፪
በዘመን መለወጫ ቅዱስ ፓትርያርኩ ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ ፱
ርእሰ ዐውደ ዓመት ........ ፬
መስቀል መድኃኒትነ ........ ፱
የማሽን ማርያም ታሪክ በአጭሩ ........ ፲
ዘመነ ጽጌ ........ ፲፪
ዜና ሊቃውንት ........ ፲፭
ጻድቃን ይወርስዋ ለምድር ........ ፲፱
እናስተዋውቃችሁ ........ ፳፪
ዜና ዕረፍት ........ ፳፱
ጤናችን (የዓይን ማዝ ትራኮማ) ........

## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጆች በመጀመሪያ ሰላምታ በማቅረብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራችሁን የተስተካከለና የተመሰገነ ለአንባብያንም የሚጠቅም ያድርግላችሁ ዘንድ ከልብ እመኝላችኋለሁ ።

ከዚህ ቀጥየ ጥያቄዎችን አቀርባለሁ መልሳቸውንም በጥሩ ሁኔታ እንደማገኝ ተስፋ አደርጋለሁ ።

፩ኛ/ አንድ መንፈሳዊ ወጣት ከአንዲት መንፈሳዊት እኅቱ ወጣት ጋር ጌታን ከሚያስከፉት ነገሮች ተጠብቆ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ሌላም ጉዳይ ቢነጋገርና አብሮም መንገድ ቢሄድ በሕገ መጻሕፍት ያስነቅፋልን ፡

፪ኛ/ ሁሉም ፍጡር በየቋንቋው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲያመሰግን ታዝዟል ነገር ግን የሰንበት ተማሪዎች መዝሙር አጥንተው ሲዘምሩ ይህ የመጤ መዝሙር ነውና እንዳትዘምሩት እየተባሉ ይከለከላሉ ለማስረጃም ከተከለከሉት መዝሙሮች ልጥቀስ እሁን ተገልጾ የድንግል ልዕልና ፡ በርሷ ላይ ያደረው ሰማዊ መና እዩት ኢየሱስን መስቀሉ ማማሩ

ለተመራመረው ብዙ ነው ምሥጢሩ

የዓለም መድኅን ቅዱስ ጌታ የተሰቀልከው በጎልጎታ ወዘተ... ናቸው ታዲያ እንደነዚህ ያሉት መዝሙሮች መጤናቸው አትዘምሯቸው እየተባሉ ወጣቶች ለምን ይከለከላሉ ?

፫ኛ በ፲፱፻፸፪ ዓ ም በ፲፱ኛ ዙር የካህናት ማሠልጠኛ ኮርስ በመቱ ተሳትፌያለሁ ነገርግን በማሠልጠኛው ውስጥ የሚደረገው አቀባበልና መስተንግዶ በቂ አይደለም ፤ ስለዚህ ትኩረት ይሰጥበት ዘንድ ለሚመለከተው ክፍል አሳስቡ እባካችሁ ፤ ልዑል እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን እያልኩ ጥያቄየን አጠቃልላለሁ የመንፈስ ቅዱስ ወንድማችሁ ዲያቆን መሐሪ ኃይሉ ከፋ ሀገረ ስብከት ቦንጋ አውራጃ

### መልስ

ዲ. መሐሪ ኃይሉ ስለ አቀረብክልን መንፈሳዊ ሰላምታ እኛም በበኩላችን ሰላምታችን እያቀረብን ለአቀረብካቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ።

በመጀመሪያ ወጣቱና ወጣቷ እየተጫዋወቱ አብረው መንገድ ቢሄዱ ቅዱስ መጽሐፍ ይከለክላል ወይ ? ስላልከው ወንድና ሴት አብረው እየተጫዋወቱ መንገድ እንዳይሄዱ የሚከለክላቸው ሕግ የለም ቅዱስ መጽሐፍም አታመንዝር ይላል እንጂ ከሴት ጋር አትነጋገር መንገድም አብረህ አትሂድ አይልም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሠማርያይቱ ሴት ጋር ብዙ ተነጋግሯል በዚያን ጊዜ ከሴት ጋር ለምን ትነጋገራለህ ብሎ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል የጠየቀው አልነበረም ብዙ ቅዱሳት አንስትንም መርጦ ከሐዋርያት ጋር እንዲማሩ አድርጓቸዋል ። ይህ ሁሉ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ እየተነበበ ወጣት ወንድና ወጣት ሴት አይነጋገሩ አብረው መንገድ አይሂዱ አይባሉም ።

በሁለተኛው ጥያቄህ አንዳንድ መዝሙሮች መጤዎች ናቸው እየተባሉ ወጣቶች እንዳይዘምሯቸው ይከለከላሉ በማለት መዝሙሮችን ጠቅሰህ ጽፈሃል እንደተመለከትናቸው የመዝሙሮቹ ቃሎቻቸው ከቤተ ክርስቲያናችን ቃላት የወጡ አይደሉም ነገርግን ዜማቸውን ስለ አልሰማናቸው ይዘመሩ ወይም መዘመር አይገባቸውም ብለን ደፍረን መልስ ለመስጠት አንችልም ። መጤዎች ያሰኛቸው የዜማቸው ቃና ይሆናል የዜማው ቃና ከተለወጠ መዝሙሩም የተለወጠ መስሎ ይገመታልና ።

—በሦስተኛውና በመጨረሻው ጥያቄህ ደግሞ በመቱ የሚገኘው ካህናት ማሠልጠኛ ለሠልጣኞች ካህናት ተገቢውን አገልግሎት የማይሠጥ መሆኑን ጠቅሰህ ለወደፊት ሥራውን በሚገባ እንዲያከናውን ለሚመለከተው ክፍል እንድናሳስብ ጠይቀሃል ጠይቀን እንደተረዳነው ማሠልጠኛው ለልማት ተግባር አመች ከሆነ ቦታ ላይ መቋቋሙ የታወቀ ነው በዚያ የሚሠለጥኑ ካህናትም ከቀለሙ ትምህርት ጋር የእትክልት አተካከልን የዘር አዘራርን የማረስንና የመቆፈርንም እንዲሁም የልዩ ልዩ እጅ ሥራ ሙያን ተምረው ።

ወደተላኩበት ቦታ ሲመለሱ የተማሩትን ትምህርት በተግባር እንዲገልጹ ነው እንጂ የዕለታዊ ምቾትን በመፈለግ አይደለም ፤ ለምሳሌ ቀደም ባለው ዘመን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በሚገባ ተምረው አውቀው ሊቃውንት ሆነው በማስተማርና በአስተዳደር ቦታ ተመድበው የሚሠሩት በድልድልና በቅምጥ የተማሩ

(ወደገጽ ፫ ይዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# እጅግ በጣም ተጨንቄያለሁ

ለጭንቀት የተለያዩ መንገዶችና ምክንያቶች አሉት ። ያልታሰበ ችግር ባልታሰበ ጊዜ ድንገት ደርሶበት ለራሱ የሚጨነቅ አለ የሚበላውና የሚጠጣው የሚለብሰው በማጣቱ የሚጨነቅም አይታጣም እንዲሁም ፀንሳ ለመውለድ የተቃረበች ነፍሰ ጡር ሴትም ተጨነቃለች ከራሳቸው አልፈው ተርፈው ስለሀገራቸው ስለወገናቸው ችግርም የሚጨነቁ አሉ ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆች ችግር ሲደርስባቸው ችግራቸውን በእርሱ አምነው እርሱን በመለመን እንዲያስወግዱት እንጂ እንዲጨነቁ ላስተማረም ራሱ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ በዚህ ዓለም ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ እየተመላለሰ ያስተምርበት በነበረው ዘመን ለቁጥር የሚያዳግቱ ብዙ ሰዎች ይከተሉት ነበር ሊቃውንት አባቶቻችን የአምስት ገቢያ ሰዎች ይከተሉት ነበር ይላሉ የአምስት ገቢያ ሰዎች ቢቆጠሩ ምን ያህል እንደሚሆኑ ግምቱን ለአንባብያን እንተውቀለን ።

እንደሰዎቹ ብዛት ፍላጉታቸውም የተለያየ ነበር እኩሉ የተራቡና የታረዙ በመሆናቸው ኅብስት አበርክቶ ያበላናል ልብስ ያለብሰናል በማለት ይከተሉት ነበር ። በደዌ ተይዘው የሚሠቃዩት ደግሞ ከየዘን ደዌ ሥጋ አላቆ በጤና እንድንኖር ያደርገናል በማለት ይከተሉት ነበር ። እንዲሁም ነብር ዳዊት "ይሚኒ ላህዩ አምውሉደ እጓለ እመሕያው" ብሎ የተናገረውን ትንቢት መሠረት በማድረግ መልኩን ለማየት የሚከተሉት ሲኖሩ በርማውያን ነገሥታት ዘንድ መንግሥታችን አስለቅቆ ይነግሥብናል የሚል ፍራቻ ስለነበር የሚያስተምረው ትምህርት ፖለቲካዊ የሆነ እንደሆነ ለገናናው ንጉሥ ቄሣር ነገረን እናስቀጣዋለን ብለው የሚከታተሉም ወገኖች ነበሩ ፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሚያስተምረው ዓለምን ለማዳን መምጣቱንና ሁሉም ለድኅነት እንዲዘጋጅ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ከክፋት ወደበጎነት እንዲመለስ ስለነበር ለተንኮል የተሰበሰቡ ሁሉ ከቄሣር ጋር የሚያጣላና የሚያጋጭ መጥፎ ነገር ባለማግኘታቸው በረጋ መንፈስ ትምህርቱን መከታተላቸውን ቀጥለዋል የዕለት ኑሯቸው ለልምላላቸው ብሎ ምን እንበላለን ፣ ምን እንጠጣለን ምንስ እንለብሳለን እያሉ ለሚጨነቁ ሰዎች የሚከተለውን ትምህርት በምሳሌ አስተምሯል ።

"ስለነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት ወይም ስለሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ አይዘሩም አያጭዱም በጎተራም አይከቱም የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል ፤ እንጂ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው ? ስለልብስስ ለምን ትጨነቃላችሁ ? የሜዳ አበቦች እንደት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ አይደክሙም አይፈትሉም ነገርግን እላችኋለሁ ሰሎሞንስ እንኳ ከዚያ ሁሉ ክብሩ እንደ አንዲቱ አልለበሰም "በማለት አስረዳቸው ማቴ ፮.፳፭ ፳፱ ። ተጨንቆ የፈለጉትን ማግኘት ማሰብ አስፈላጊ መሆኑ ቢታወቅም መጨነቅ ተገቢ አይደለም በሕይወተ ሥጋ እስከአለ ድረስ እንደማይቻል የማያጠራጥር ነገር ነውና በዚህ ዓለም ላይ የሚኖር ሰው መጨነቁን አያቋርጥም ከራሳቸው ይልቅ ስለቤተሰባቸው ስለጉረቤቶቻቸው ስለሀገራቸው ስለወገናቸው የሚጨነቁ አንዳንድ ሰዎች ሲኖሩ ከራሳቸው በስተቀር ስለሌላው ደንታ የሌላቸው ደግሞ የሚያስቡት ለራሳቸው የሚጨነቁት ለግል ኑሯቸው ነው ።

ከዚህም የተነሣ ልመናቸው በፈጣሪ ዘንድ ተሰምቶ ግዳጃቸው ሊፈጸምላቸው አይችልም እግዚአብሔርንም እንደማያይ እንደማይሰማ አድርገው ይገምቱታል ። ስለዚህ ነቢዩ ዳዊት "ዘፈጠራሁ ለዓይን ኢይሬዕዩኑ ወዘተከላሁ ለዕዝን ኢይሰምዑኑ" ዓይንን እንዲያይ የፈጠረ አምላክ አይመለከትምን ጆሮንስ እንዲሰማ አድርጎ ያዘጋጀ ፈጣሪ አይሰማምን ብሏል ።

ነቢዩ ዳዊት በግ ከሚጠብቅበት ተመርጦ ለሕዝብ መሪ መሆኑ የታወቀ ነው ሕዝቡን እያስተዳደረ ሳለ ሕዝቡን ይቆጥር ዘንድ ሰይጣን አነሣሣው የቅርብ አማካሪውና ታማኝ አሽከሩ ኢዮአብ ሕዝቡን ከመቁጠር እንዲከለከል መላልሶ መከረው ዳዊት ግን ምክሩን ሰምቶ በሥራ ላይ ለማዋል አልፈለገም



የኢዮአብ ምክር በእርሱ ዘንድ የተናቀ ሆነ "የሚጠፉ ከተማ አዋጅ ቢነግሩ አይሰማ" እንደሚባለው ዳዊት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሕዝቡን በመቁጠሩ ሦስት መቅሠፍቶች ታዘዙበት እነርሱም ፩ኛ የሦስት ዓመት ረኃብ ፤ ፪ኛ/ ለሦስት ወራት በጠላት ጦር መወጋትና መባረር ፫ኛ/ ለሦስት ቀናት መቅሠፍት ናቸው እነዚህን ሦስት የመከራ ወሬዎች እንዲናገር የተላከው ጋድ የተባለው ነቢይ ነበር ከሦስቱ መከራዎች አንዱን መርጦ እንዲነግረውና ለላከው መልሶ እንዲናገር ነቢዩ ጋድ ጠየቀው።

ዳዊትም በሁሉ ተጨንቄያለሁ ነገር ግን በሰው እጅ ከምወድቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻለኛል ብሎ የሦስት ቀኑን መቅሠፍት መረጠ ወዲያው ቀሳፊ መልአክ መጥቶ ከሕዝቡ ፸ሺ ሰዎችን ገደለ።

ነቢዩ ዳዊትና ሽማግሌዎች ማቅ ለብሰው በግንባራቸው ተደፍተው ልመናቸውን ወደፈጣሪ አቀረቡ ዳዊት የሕዝቡ በመቀሠፍት መመታት እጅግ በጣም ስላሳዘነው ሕዝቡ እንዲቆጠሩ ያዘዝኩኝ እኔ ነኝ እነዚህ ሕዝቦች ምን በደሉ ፤ አሁንም አምላኬ ሆይ ! እጅህ በእኔና በአባቴ ወገኖች ላይ ትሁን በማለት ወደፈጣሪው ልመናውን አቀረበ እግዚአብሔርም የሕዝቡን ዕልቂት ተመልክቶ ተጸጸተ ቀሣፊ መልአኩን እጅህን ከመቀሠፍት መልስ አለው ዳዊትም ኦርና በተባለው ሰው አውድማ መሥዋዕት አቀረበ ። እግዚአብሔርም መሥዋዕቱንና ጸሎቱን ተቀብሎ መዓቱን ወደ ምሕረት ቁጣውን ወደትዕግሥት መልሶለታል ። ይህም እግዚአብሔር በጸሎት በንስሐ በመሥዋዕት በሀገር ላይ የታዘዘውን መቅሠፍት ለባርና ቸነፈር እንደሚያስወግድ ታላቅ መረጃ ሊሆን ይችላል ፩ኛ ዜና መዋዕል ፳፩ ፲፬—፳፯ ።

መቅሠፍት በልዩ ልዩ ምክንያት በሀገር ላይ ሊታዘዝ ይችላል ። ሕዝቦችም ሳያስቡት ድንገት መዓት ይታዘዝባቸውና ይቀሠፋሉ ፤ የተቃጣውን መዓት ወደምህረት እንዲመለስ ለማድረግ ደግሞ ጸሎትን ምህላን መሥዋዕትን በንጹሕ ልቡና ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ነው ፤ ኖኅ በመርከብ ውስጥ ሆኖ ከጥፋት ውሀ ከዳነ በኋላ ከመርከብ ሲወጣ ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገርና ወደፊትም ሊያደርገው ስለሚገባው ነገር የተነገረውና ሁለተኛም እንደማየጠፋው የቃል ኪዳን ምልክት ሦስት ኅብር አረንጓዴ ፤ ቢጫ ፤ ቀይ ምልክት ያሳየው በመሥዋዕትና በጸሎት አማካይነት ነው (ዘፍ·፱–፲፫)

ከላይ ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ከአምላኮተ እግዚአብሔር ጋር የሚቀርበው ፡ ጸሎት የሚሠዋው መሥዋዕት እግዚአብሔር አምላክን ከመዓት ወደ ምህረት እንዲመለስ ለሕዝቡ እንዲራራና ይቅርታም እንዲያደርግ ያደርገዋል ።

ራሱ ጌታችን "ለምኑ ይሠጣችኋል ፈልጉ ታገኛላችሁ ደጅ አንኳኩ ይከፈትላችኋል የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልግም ያገኛል መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል "ብሏል ማቴ. ፯.፯

ስለዚህ በደረሰውና በሚደርሰው ችግር ሁሉ ከመጠን በላይ መጨነቅና መጠበብ ሳይሆን የሚያቀርቡትን መሥዋዕት የሚጸልዩትን ጸሎት በንጹሕ ልቡና በትሁት ሰብእና ሆኖ ማቅረብ ያስፈልጋል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምር "ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ" ብሏል ዮሐ.፲፬.፩

እንግዲህ ሁላችንም እንደ ዳዊት ያልታዘዝነውንና ያልተፈቀደውን ፈጽመን እጅግ በጣም ተጨንቄያለሁ ከማለት ይልቅ በእግዚአብሔር አምነን ወደ እርሱ እንጸልይ እስመ በጸሎተ ጻድቅ ትድኅን ወኢትማስን ሀገር በጻድቅ ሰው ጸሎት ሀገር ከመቅሠፍት ትድናለች አትጠፋም ተብሎ ተጽፎአልና ።

## ደብዳቤዎች ...

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ሳይሆኑ ከውሻ ጋር እየታገሉ ጦማቸውን እየዋሉና እያደሩ ጥሬ እየቆረጠሙ በቀሰሙት መንፈሳዊ ዕውቀት ነው ።

የሚሠለጥኑትም ካህናት መመልከት ያለባቸው በማሠልጠኛው የሚሠጠውን ትምህርት ነው እንጂ ጊዜያዊ ጥቅምን መሆን የለበትም እንዲሠለጥኑ ጥሪ የሚደረግላቸውም ተምረው በሥራ ላይ እንዲያውሉት ነው እንጂ በኮርስ በቆዩበት ጊዜ እንዲመቻቸው አይደለም ።

ስለዚህ ትኩረት ይደረግበት ተብሎ ሊጠየቅ የሚገባው ለአቀባበሉና ለመስተንግዶው ሳይሆን በትምህርት አሰጣጥ በኩል ጉድለት እንዳለበት ነው ለጊዜያዊው ምቾትና አቀባበል ግን ጥያቄ መቅረቡ አግባብ አይመስለንም ።



www.ethiopianorthodox.org

# በዘመን መለወጫ ቅዱስ ፓትርያርኩ ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

በከተማና በገጠር በየብስና በባሕር ያላችሁ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበር ያገርን አንድነት የወገንን ደኅንነት ለመጠበቅ በየጠረፉ የምትገኙ በሕመም ምክንያት በየሆስፒታሉ ያላችሁ። እንደዚሁም በዚህ ሰዓት በልዩ ልዩ ቦታና ሥራ ላይ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የዘመናት ባለቤት እግዚአብሔር እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ (ከ፲፱፻፹፬ ወደ ፲፱፻፹፭ ዓ.ም) በሰላም አሸጋገራችሁ ።

“ወኢንትሀከይ ገቢረ ሠናይ እስመ በዕድሜሁ ነአርር አምጣነ ብነ ዕለት ንግበር ሠናየ ለኵሉ :”

በጎ ሥራ መሥራትን ቸል አንበል በጊዜው እናገኘዋለንና ጊዜ ሳለን ለሁሉም መልካምን እንሥራ” (ገላ ፮፡፱ ፲)

ዘመን ወይም ጊዜ ሲያልፍ በዓይን አይታይም ካለፈ በኋላ ግን መልካም ለሠሩበት በደስታ ፤ ላልሠሩበት በጸጸትና በኀዘን ይታወሳል ። ያለፈንም ጊዜ ወደኋላ ተመልሶ ማንም ብልህ ወይም ጥበበኛ ሊይዘው የሚችል አይደለም ። ነገር ግን ያለውንና የሚመጣውን ማለት ዛሬንና ነገን በጠዋት የሚነሡና ለመልካም ሥራ የሚተጉ በሥራ ይይዙታል ። እንደሚገባም ይጠቀሙበታል ። በጠዋት የማይነቁና እስከ ቀትር የሚተኙ ግን መምጣቱንና መኖሩን ሳያውቁ ማለፉን ብቻ ይረዳሉ ። ለቸልተኝነት ኑረዋልና ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

የሥራ ጊዜና የሕይወት ዘመን በጣም አጭር ስለሚሆን ፈጥኖ ያልፋል ። ሰከንድ በደቂቃ ፤ ደቂቃ በሰዓት ፤ ሰዓት በዕለት ፤ ዕለት በሳምንት ፤ ሳምንት በወር ፤ ወር በዓ[illegible] ሲያ

ልፍ ዱካው አይሰማም ። ፍለጋውም አይታይም ። ዱካውን ሊሰሙ ፍለጋውንም ሊያዩ የሚችሉ ቢኖሩ በሥራ ያሳለፉትና መልካም ውጤት ያገኙበት ብቻ ናቸው ።

እነርሱም ያለፈውን ጊዜ ሠርተውበታልና መልካም ውጤትም አይተውበታልና በማለፉ አያዝኑም ፤ አይጸጸቱም ። አዲስ የሚመጣውን ዓመት በሥራ ለመቀበል ይዘጋጃሉ እንጂ ።

አንዳንድ ሰዎች ግን የጊዜን ፈጣንነት የሚያስተውሉት አይመስሉም ። ምክንያቱም የየዕለት ተግባራቸውን በጊዜው ከማጠናቀቅ ይልቅ ነገ እናደርገዋለን ማለትን ሲያዘወትሩ ይታያሉና ። በዚህ ምክንያት “ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ” የሚለውን አምላካዊ ቃል የዘነጉ ሁነው ይታያሉ ። (ማቴ ፮ ፡ ፴፬)

በዓለም ለሚኖር ሰው ምንም ቢሆን ከጊዜ የበለጠ ውድ ነገር አይኖረውም ። ይኸውም ደቂቃን በደቂቃ ፤ ሰዓትን በሰዓት ፤ ተቆጣጥሮ በመልካምና በጠቃሚ ሥራ የሚያሳልፍ ትጉህ ሰው ቢኖር እርሱ ጊዜን ይዞታል ። በከንቱም አላሳለፈውም ። በጊዜና በዘመን ተግቶ የማይሠራ ግን ጊዜው ካለፈ በኋላ የሚያየው መልካም የሥራ ወጤት ሲያጣ በብርቱ ኀዘን ላይ ይወድቃል ።

ስለዚህ ጉዳይ መጽሐፍ እንዲህ ይናገራል ።

“በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን?

ወራቱም እንደምንደኛ ወራት አይደለምን?

አገልጋይ ጥላ እንደሚመኝ ፤ ምንደኛም ደመወዙን እንደሚጠብቅ እንዲሁ ነው (ኢዮ ፯ ፡ ፩ – እነሆ ዛሬ ያለንበት ዘመን የሥራ እንጂ የዋዛ የፈዛዛ ዘመን አይደለም በዚያውም ላይ ቀኑ እየከፋ ፤ ሥራው እየበዛ ፤ ለመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ በብዛት እየተጠየቁ መጥተዋል ። ስለዚህ በማንኛውም የሥራ ቦታ የተሰለፈ ሁሉ በጥበብና በማስተዋል ተሞልቶ በሥራ በመወሰን አጭርና ውድ ፈጣንም የሆነውን ጊዜ በሥራ ላይ ማዋል ይኖርበታል ። ጊዜና ሥራ እርምጃን ይለውጣል። በየቀኑ ያለፉትን ጊዜያት ብንመለከት ብዙ ሰዎች ጊዜያቸውን በመልካም ሥራ ላይ አውለውት አልፈዋል ። በጽድቅና በታሪክም ተመዝግበውበታል ።

በፊታችን ያለው ጊዜ አጭር ቢሆንም ውድ ነው ። ጊዜ ጠቅላላ የሕይወታችን መሠረት ነው ። ጊዜን በመልካም ሥራ ብናውለው እንጠቀማለን ። በከንቱ የሚያጠፉትን ደግሞ በከንቱ ይዞ ይጠፋል ። ጊዜ የገንዘብም የሕይወትም ራስ ነው ። ማለት ሠርቶ ለመክበር ተምሮ ለማወቅ መሣሪያው ሰላምና ፀጥታ የሰፈነበት ጊዜ ነውና ።

በልዩ ልዩ ምክንያት ያለሥራ ያለፈ ጊዜ ተመልሶ ሊገኝ አይችልም ሌሎች ነገሮች ግን ካለፉና ከጠፉ በኋላ ሊገኙ ይችላሉ ። ለምሳሌ ጤና ቢታጣ በሀኪሞች ዕርዳታና በልዩ ልዩ መድኃኒት በእግዚአብሔር አጋዥነት መልሶ ጤንነትን ማግኘት ይቻላል ፤ ገንዘብ ቢከስር በርትቶ በመሥራት የጠፋው ይተካል ። መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግዴታዎችን ለመፈጸም በጊዜ መጠቀም ያስፈልጋል። ጊዜን በከንቱ ላለማባከንና በጠቃሚ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ነገሮች አሉ ። እነርሱም ትጋት ንቃት ጥበብ ትዕግሥት ማስተዋል አለመሰልቸት እና ሁልጊዜ መሥራት ናቸው ። እነዚህ ጊዜ በከንቱ እንዳያልፍ የሚረዱ የጊዜ መሣሪያዎች እንደሆኑ ይታመናል ።

የጊዜ ባለቤት እግዚአብሔር ጊዜን የሰጠ የሰው ልጆች በተሰጣቸው ጊዜ መልካም ሥራ ሊሠሩበት ነው እንጂ ያለሥራ ሊያሳልፉትና እንዲሁ ቁጭ ብለው ሲመሽና ሲነጋ ብቻ ሊመለከቱት አይደለም ።

ጊዜንና ዘመንን ሰዎች ያለሥራ ቢያሳልፉአቸው እነርሱም እነሱን ያለክብር ያሳልፏቸዋል ። የሚሠሩባቸውን ግን ያከብሯቸዋል። ስም አጠራራቸውንም በክብር የታሪክ ማኅደር ያስመዘግቧቸዋል ።

ስለሆነም ጊዜን ሰዎች ያለሥራ በስንፍና ፤ ያለጥበብ በድንቁርና እንዲያሳልፉት አልተፈቀደም ። በጥበብ ሊመላለሱበት ሠርተው ሊከብሩበት ፤ ጊዜን ከሰላም ጋር የሰጠ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑበት ነው እንጂ ስለዚህ ጊዜው ሳያልፍ ቀኑ ሳይመሽ ራስንና ወገንን የሚጠቅም ሥራ ሠርቶና ስም አጠራርን በሕይወት መጽሐፍ አስመዝግቦ ማለፍ ይጠቅማል ። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አለ “አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንደምትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ። ቀኖች ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ ።

ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን እወቁ ... ሌሊቱ አልፎአል ቀኑም ቀርቦአል እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ” (ኤፌ ፭ :



www.ethiopianorthodox.org

፲፬—፲፯) (ሮሜ ፲፫ ፡ ፲፩—፲፫)

ጊዜን በከንቱ ሳያሳልፉ በጠዋት ተነስተው ያለእርሱ ፈቃድ ፡ ያለእርሱ አስፈጻሚነት ምንም ሥራ ሊሠራ አለመቻሉን አውቀው በእምነት ወደእርሱ በመቅረብ የምንሠራውን መልካም ሥራ ሁሉ ከመልካም ፍጻሜ ለማድረስ እንችል ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልን ጊዜያችንም የሰላምና የፍቅር እርስ በእርሳችን ተግባብተን የምንሠራበት እንዲሆን ባርክልን በማለት ለሚለምኑት ሁሉ ያበራላቸዋል ። ሲታመሙ የሚፈውስ ፡ ሲደክሙ የሚያጽናና ፡ ሰላምን ሲያጡ ሰላምን ፡ ፍቅርን ፡ አንድነትንና እርቅን የሚያድል ቅዱስ መንፈሱን ያሳድርባቸዋል ።

ሰላም የተሞላ ጊዜ ታላቅ በረከትና ስጦታ ነው ስጦታነቱም ከእግዚአብሐር ለሰው ልጆች የታደለ ነው ። በረከትነቱንና ስጦታነቱን ተገንዝቦ በሚገባ የማይሠራበት ቢኖር የእግዚአብሔርን በረከትና ስጦታ በከንቱ አባክኗልና ሳይቀጣ አይቀርም ።

በየንዳንዱ ሰው ሕይወት የተለያየ የሥራ ጊዜ አለ ። ለተማሪው የመማሪያና የጥናት ጊዜ አለው ፡ ለገበሬውም የመዝሪያና የመሰብሰቢያ ጊዜ አለው ለነጋዴውም የመግዣና የመሸጫ ጊዜ አለው ። ነገር ግን የመማሪያው ጊዜ ከጥናቱ ጊዜ ልዩ ነው ፡ እንዲሁም የመዝሪያው ወቅት ከመሰብሰቢያው ፡ የመግዣው ወራት ከመሸጫው ልዩ ነው ። ሁሉም በየጊዜው ጊዜውን ከሥራው ፡ ሥራውንም ከጊዜው ጋር በማገናኘት የሥራ እንደሆነ መልካምና አጥጋቢ ውጤትን ያስገኛል ።

በዚህ በምንቀበለው አዲስ ዓመት ስለሀገራችን ሰላምና አንድነት ፡ ስለሕዝባችን ደኅንነት ጠንክረን መሥራትና ያጣነውን መልሰን እንድናገኝ ፡ የፈረሰውን እንድንገነባ ዘመኑ የሰላምና የፍቅር ዘመን እንዲሆንልን አዘውትረን እንጸልያለን በትጋትም እንሠራለን ።

ስለሀገራችን ሰላምና አንድነት ስለሕዝባችን ሕይወት ልናስብ ፡ ልንጸልይና እግዚአብሔርን ልንለምን ግዴታ አለብን ። ኢትዮጵያውያን ሁሉ ስለሀገራቸው አንድነት ፡ ስለየራሳቸው ሰላምና ደኅንነት እንዲያስቡ ፡ እንዲጸልዩና እግዚአብሔርን እንዲለምኑ ፡ አንዱ የሌላውን ሕይወት ለማትረፍ በጎ አመለካከት እንዲኖረው ማስተማር ይገባል ።

እግዚአብሔር የሰላም ዘመንን ሊሰጥ ፡ አንድነትን ሊያጸና ፡ ሥራን ሊባርክ የሚፈቅደው ደግሞ ሰዎች ሁሉ ከኀጢአት ወደ ጽድቅ ፡ ከክፋት ወደ በጎነት ፡ ከክህደት ወደ ሃይማኖት ፡ ከጥላቻ ወደፍቅር ፡ ከመለያየት ወደ አንድነት ሲመለሱ ስለሆነ ሰዎች ተንኰልን ሁሉ ትተው ወደ በጎነት እንዲመለሱ ማስተማር የካህናትና የሃይማኖት ሰዎች ሁሉ ተግባር ነው ። ኃጢአት ፡ ግፍና በደል በበዛ ቁጥር ሰላም እየጠፋ ጦርነት እየተስፋፋ መቅሠፍትና ፍጅት እየከፋ ይመጣል ።

በአሁኑ ጊዜ በሀገራችንም ሆነ በዓለም ላይ በአንድ በኩል በድርቅ በአባርና በቸነፈር በሌላ በኩል ደግሞ በጦርነት የሰዎች ሕይወት እንደቅጠል እየረገፈ ይታያል ።

በዚህ በሚመጣው አዲስ ዓመት እግዚአብሔር ሰላሙንና ፍቅሩን እንዲያወርድልን ፤

የሀገራችንን አንድነት እንዲያጸናልን ፤

አዝመራውን እንዲባርክልን ፤

ዘመኑን የሰላም ዘመን እንዲያደርግልን ፈቃዱ ይሁንልን ።

የዘመናት ባለቤት እግዚአብሔር ዘመኑን የደስታ ዘመን ያድርግልን ።

ለሀገራችን አንድነትን ለሕዝባችን ፍቅርንና መተሳሰብን ይስጥልን ።

ለዓለምም ሁሉ ፍቅርንና አንድነትን ያድልልን ።

አሜን

# እናስተዋውቃችሁ

(ከገጽ ፳፪ የዞረ)

ወላጆቹ ወስደውት አባ ውዱ የተባሉት መነኩሴ አጼ ገብረ መስቀል በሰጡት የእጅ መሳለሚያ መስቀል ዓይኑን ቢያሻሹት በራለት ይህም በቅርብ ቀን የተፈጸመ ተአምር ነው ። እንግዲህ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ይህንን ተአምረኛ ታቦት ሊያውቁና ሊረዱት ሊሳለሙትም ይገባል ለዚህ ነው ሕዝቡ ሲለምነው የሸዋን ቅዱስ ጊዮርጊስ ግንድ አንሴ አሞራ ቀልቤ ብር በእንቅቡ ንብ በዱሩ ዕውር አብራው እያሉ የሚለምኑት እስከ አሁን ድረስ የሸዋንን ቅዱስ ጊዮርጊስን ገንዘብ ሰርቆ ወይም ደመወዜ ነው ብሎ ስእለት የገባውን ንብረቱን ገንዘቡን የወሰደና የተጠቀመ ሰው የለም ከወሰደም ከላይ እንደተገለጸው ይሆናል ፲፱፻፹፯ ዓመቱ ሲሆን ዘበኛው ንብ እንጂ ሰው አይደለም ይህም ከፍተኛው ተአምር ነው አሁንም የተጨነቀውን ሁሉ ይረዳል ለሁላችንም ከሰማዕቱ ረድኤት በረከትን ያሳትፈን አሜን ።

የዜናው አቅራቢ ሊቀ ብርሃናት
መርቆሬዎስ አረጋ

# ርእሰ ዐውደ ዓመት

ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ

ርእሰ ዐውደ ዓመት ማለት የዓመት ዙር መጀመሪያ ማለት ነው ምክንያቱም ፀሐይ በምዕዋዴ ማለትም በራሷ መዞርያ በመዞር የዓመት ጉዞዋን ጨርሳ የሚቀጥለውን የዓመት ዙርያዋን ጉዞ እንደገና የምትጀምረው በመስከረም አንድ ቀን ስለሆነ ቀኑ ርእሰ ዓውደ ዓመት ተባለ ። ለምሳሌ አንድ ልጅ በማኅፀን የሚኖረውን የዘጠኝ ወር ከምስት ቀን እድሜ ፈጽሞ ሲወለድ መታዩት የሚጀምረው ወይም መጀመሪያ የሚታየው ራሱ ስለሆነ በዚህ አንፃር ዕለቱ ርእሰ ዐውደ ዓመት ተባለ ። እነሆ ፍጥረት ሁሉ በሠራዒውና በመጋቢው እግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ወጣበት የማይመለስ የለም ። ይህንንም ስሎሞን በሠፈው ያስረዳል ።" ፀሐይ ትወጣለች ፀሐይ ትገባለች ወደም ትወጣበትም ሥፍራ ትመለሳለች (ትቶ ኩላለች) ።

ነፋስ ወደ ደቡብ ይሄዳል ፡ ወደ ሰሜንም ይዞራል ዘወትር በዙረቱ ይዞራል ። በዙረቱም ደግሞ ይመለሳል ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ ባሕሩ ግን አይመላም ፡ ፈሳሾች ወደሚሄዱበት ሥፍራ ወደዚያ ይመለሳሉ ፡ ሰውን ቅሉ ሳይቀር አፈር ነህና አፈርም ትመለሳለህና ፡ ወደመጣህበት መሬት እስከትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ ብሎታል (ዘፍ. ፫ ቁ ፲፱ መክ ፩ ቁ ፭—፰ እንግዲህ በፀሐይ ዙርያ የሚዞሩ ከዋክብቶች (ፕላኔቶች) እንዳሉ ፡ ፀሐይ በምድር ዙሪያ ምድርም በፀሐይ ዙሪያ ትዞራለች ።

አራቱ ወቅቶችም የሚፈራረቁት የጠፈር አካል በሆኑት ፍጥረቶች ዑደት አማካይነት ነው ። አራት ወቅቶች የተባሉትም መፀው ሐጋይ ፀደይ ክረምት ናቸው መፀው ማለት ጥቢ ሳተን መኸር ማለት ነው ምክንያቱም የነፋስ ወቅት በመሆኑ አዝርዕቶች አትክልቶች በነፋስ ግፊት እየተወዛወዙ አድገው በፀሐይ ሙቀት አብበው አፍርተው ፍሬያቸውን ለዘር፣ ለአትክልተኛው ቆፋሪ ስለሚያበረክቱ ነው ሐጋይ ማለት በጋ የደረቅ ወራት ማለት ነው ምክንያቱም ምድር የለበሰችው ለምለም ሣር ደርቆባት ከልምላሜ ተራቁታ በአፈርነት ገጽታ ስለምትታይ ነው ።

ፀደይ ማለት በልግ (በላጊ) ማለት ነው ምክንያቱም አልፎ አልፎ ዝናም ስለሚዘንም የደረቀው ሣር ራሱን ብቅ ብቅ እያደረገ ስለሚበቅል ያንን የበልግ ጨፈ የቀመሱ ጥጆዎች (ጥጆች እንቦሶች የፈረስ ግልገሎች ስለሚፈነጥዙና ስለሚዘሉ የሚቦርቁበት በመሆኑ (በልግ) ተብሏል ። ክረምት ማለት የውሃ ወራት ማለት ነው ፡ ኃይል አጥተው የነበሩት ወንዞች ኾረቶች ፈሳሾች ሁሉ ኃይል አግኝተው የሚደነፉበትና ኃይላቸውን የሚያሳዩበት ወቅት ስለሆነ አዝርዕት አትክልትም በብዛት የሚዘሩበት የሚተከሉበት ቡቃያና ዛላ የሚያሳዩበት ስለሆነ ይህን ሁሉ ለውጥ የሚያገኙት በዝናብ አማካይነት በመሆኑ ወርኃ ማይ ተብሎአል ። (ማር ፬. ቁ ፳፰) ሊቁ ባስልዮስም ወጠይቅ ሥርዓተ ፀሐይ ወከዋክብት ዘከመ እፎ ይትቃረቡ ወዘከመ እፎ ይትራኅቁ በበይናቲሆሙ ፀሐይን ጨረቃንና የከዋክብትን ሥርዓት እወቅ ተረዳ ፀሐይና ጨረቃ በሕፀፅ እንዴት እንደሚቀራረቡ ማለት ጨረቃ ማታውን ሠርሖት ልታደርግ ፩ድ ቀን ሲቀራት ስሌዳዋ ፀሐይን ሲከተል ይውላል በምትጠልቅበት ጊዜ ፯ኛ እጅ ብርሃኗን ለኵሰባት ትጠልቃለች። እስከ ፲፭ ሌሊት ብርሃኗ እያደገ እየጨመረ ይሄዳል ከሥራ አምስት ቀን በኋላ ብርሃኗ እየተቀነሰ ሕፀፅ እያደረገች ትሄዳለች በምልዓት እንደምን እንደሚራራቁ እወቅ ማለትም ፀሐይ በምዕራብ ተፈጥሮ አራት ኪክሮስ አብሮት ሲጠልቅ ጨረቃ በምልዓት ስታበራ አድራለችና ሃይም ፴፫ ክፍል ፈቱ ፲፯ ፲፰ መዝ ፶፫ ቁ ፲፱ ብሎአል።

ይህንንም የጨረቃን ሁኔታ በምሥጢር መምህራን ለዮሐንስ መጥምቁ ምሳሌ አድርገውታል ። ምክንያቱም ጨረቃ ከፀሐይ በተለይ ፲፭ ቀን ሙሉ ብርሃን በመስጠት ቆይታ ከሥራ አምስት ቀን በኋላ ሕፀፅ እንደምታደርግ የዮሐንስ መጥምቅም ራስ ከእካሏ ከተለየች በኋላ አሥራ አምስት ዓመት ዞራ አስተምራ አርፋለችና በሌላም ትርጓሜ ወእስርአየት ብእሲት እንተ ትለብስ ፀሐየ ወወርኃ ታሕተ እገሪሃ እመቤታችን ፀሐየ ጽድቅ ክርስቶስን ፀንሳ ታየች ዮሐንስ መጥምቅም ሰገደላት ተብሎ ስለተነገረለትና ለጨረቃ የዓመት ዙሪያ መንገድ ተመሳሳይ ስለሆነ የዘመን መለወጫችን በዕለተ ዮሐንስ እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን ወሰነች ። ራእ.፲፪ ቁ ፩ ።

በሌላም መልኩ ዮሐንስ መጥምቅ "እነሆ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ መንገድህንም በፊቱ ያስተካክላል" ሚክ. ፫ ቁ



www.ethiopianorthodox.org

ማር ፩ ቁ ፱—፲ ተብሎ ትንቢት የተነገረለት እንደመሆኑ ለዘመነ ኦሪትና ለዘመነ ወንጌል ወይም ለብሉይና ለአዲስ ዘመን መገናኛ መሥመር መተላለፊያ በር ነበር ። ለምሳሌ አንድ በር ለሚወጣው መውጫ ሲሆን ለሚገባው ደግሞ መግቢያነቱ ግልጽ ነው የፍጻ —የኩነኔ ዘመን የነበረው ክፍለ ዘመን ሲፈጸም ዓመተ ምሕረት የይቅርታ ዘመን መክፈቻ ቀን ሲቃረብ ዮሐንስ መጥምቅ የንስሐ አዋጅ ነጋሪ የወንጌል አብሳሪ ሆኖ በመምህርነት ተነሥቶ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ስለለወጠና ስለመለሰ የዘመን መለወጫም በዮሐንስ ቀን እንዲሆን ተወሰነ ።

የትምህርቱም ርእስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ የእግዚአብሔርን ጐዳና ጥረጉ ጥርጊያውንም አስተካክሉ ፡ እያለ የሰውን ልብ ለእግዚአብሔር ንጹሕ ማደሪያ ለሕገ መመላለሻ ጥርጊያ ለማድረግ ያውራ ጐዳና ባለ ሥልጣን እና የጥዳት ሹም ነበረ ለማለት ያስደፍራል (ኢሳ ፵ ቁ ፫ ፬) እንግዲህ ዮሐንስ በሰው ልብ በትሎ ሥር ሰዶ የነበረው የኃጢአት የባዕድ አምላክ አራሙቻ ተነቃቅሎ እንዲጠፋ ንጹሑ የአምልኮተ እግዚአብሔር ፍሬ በሰው ልብ እንዲነሠራፋ ጥረት የሚያደርግ ትጉህ መንፈሳዊ ሠራተኛ ነበረ በጊዜውም የነበረው ትውልድ በዮሐንስ ነጋሪት ኃጢአትን በመናዘዝና የንስሐ ጥምቀት በመጠመቅ ብዙ የጥፋት ለውጥ ስለተደረገ የዘመን መለወጫችንም በዮሐንስ ዕለት ሆነ ።

እንግዲህ አዲሱን ዘመን ሉቃስን ተረክበናል ዓለም እንደባሕር ሲሆን ዘመን ደግሞ እንደመርከብ ስለሆነ ምድራዊውን ፍጥረት እንግር ተሸክሞታል ሁላችንም እንደ ባሕር በተንጣለለው ዓለም... የምንመላለሰው የሕይወት ዘመናችንን መርከብ አድርገን ነው ግን ቀዛፊውና አሻጋሪው የዘመናት ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ በባሕር የተመሰለ ዓለሙንና በመርከብ የተመሰለ ዘመንን አስማምቶ የሚያስኬደው የዘመን ባለቤት እግዚአብሔር ነው ፡ እርሱ ነው ከዘመነ ማርቆስ ወርደን ወደ ዘመነ ሉቃስ ስንሻገር ለባለመርከቡ ማለትም የዘመናትን ለውጥ ላደረገና ለሚያደርግ ልዑል እግዚአብሔር ምን ዋጋ ከፍለንዋል ፡ የከፈልነው ክፍያ አለን ? ምንም ቢሆን ለሚመላለስበት ዕድሜው ዋጋ የከፈለው ፍጡር የለም ። ፍጠረን ሳንለው አስቦ እንደፈጠረን ዘመንና ወራትንም የሚበቃንን ያህል በረቂቅ ጥበቡ በሰፊው ሐሳቡ አስቦ ከዚህ እስከዚህ በማለት ወስኖ በነፃ ይሠጠናል እንጂ ከቶ አንዳች የእድሜ ዋጋ አይጠይቀንም ፡ የሐዋ. ፲፯ ቁ ፳፮ ፳፯ ግን የምንጠየቀው አንድ ነገር አለ እርሱም በዚህ ዓለም የምንኖርበት እድሜ ሥራ ልንሠራበት የተሠጠን መሣሪያ ስለሆነ በተሠጣችሁ ዘመን ምን ሠራችሁ ወይንስ ነበራችሁ ፡ ተብለን ነው የምንጠየቀው ልዑል እግዚአብሔር ይጠይቃል መባሉም የሠራነው ምን ዓይነት የነበርንበት ወይንስ እንደሆነ የማያውቅ ሆኖ አይደለም ፡ ሲያውቅ የሚሞግት ዳኛ እንደ ተባለው ያቤቶች ምሳሌ ስሕተታችንንና ሕገ ወጥነታችንን ከቃላችን አሳምኖና አስመስክሮ ለመውቀስ የተፈረደው አግረ ለማስናት ነው እንጂ የሠራነው ሲሠወረው ቀርቶ (አሳባችንን እንኳ ከመታሰብ አስቀድሞ ያውቀዋል ። ነቢዩ ኢሳይያስ ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል ፡ ይቅርታውም ብዙ ነው ፶፭ ቁ ፯ እንዳለ በደለኛ ሁሉ ዘመን እንደተለወጠ ባለፈው ዓመት መጥፎ ሥራ የሠራ ቢኖር የሠራችም ብትኖር መጥፎ ልማዱን ትቶ በለውጡ ስነ ምግባሩን ያማምር ታማምር ሕገ ወጥ የሆኑ ወንዶች ሴቶችም ያሉ እንደሆነ ከየኑሮ ጓደኞቻቸው ጋር በሕግ ተባብረው በንስሐ ታድሰው በቁርባን ተዋሕደው ይኑሩ ባለፈው ዓመት የጠብ ክርክር ቅርስ ያለው ቢኖርም የጠብ ክርክሩን ሐብል በዕርቅ ቆርጦ በሰላም በፍቅር ተግባብቶ ይኑር ይህ የሆነ እንደሆነ በተሠጠን ዘመን ሠራንበት ማለት ነው ምን ሠራችሁ ተብለን ከፈጣሪያችን ለሚቀርብልን ጥያቄ መልስ አናጣም በሥራችንም አናፍርበትም ፩ ዮሐ ፪ ቁ ፳፰ ባለፈው ጊዜያችን የሚያማፍር ሥራ ሠርተንበት እንደሆነ በሕሊና ዳኝነት ተፈርደን በደላችንን አምነን በማስወገድ በንስሐ አስወግደን ወደፊት ያለውን ጊዜያችንን ለተቀደሰ ክርስቲያናዊ ተግባር እናውለው የንስሐ ፍሬ አፍርተን ለፈጣሪያችን እናበርክተው በእግዚአብሔር ዘንድ የሚፈለግብን ቦረንትቻ ከጨሌሉ ከአድባር ቆሌ ያልተቀላቀለ ንጹሕ አምልኮት ንጹሕ ስነ ምግባር ብቻ ነው ፡

ስለዚህ ዘመኑ እንደ ተለወጠ የውሥጥ ሁኔታችሁን ሕጋዊ በሆነ መንፈስ ፍሬ ለውጡ ፡ ንስሐ በመግባትና በመታደስ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በመቀበል ወደ ልዑል እግዚአብሔር ቅረቡ ጊዜያትንና ዘመናትን የሚለውጥ ዳን. ፪ ቁ ፳፩” እግዚአብሔር አምላካችን የሚወደውን ሥራ ሠርተን ለቃሉም ታዛዦን የክብሩ ተካፋዮች የመንግሥቱ ወራሾች እንሆን ዘንድ በቸርነቱ ሁላችንን ይርዳን አሜን ።



# መስቀል መድኃኒትነ

ሰማይን ከነግሡ ምድርን ከነግግን ግሡ የፈጠረ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑና የሰውን ሥጋ ከመልበሱ አስቀድሞ በመስቀል ተሰቅየ ሙቻና ራሴን መሥዋዕት አድርጌ አድንሃለሁ ብሎ ለመጀመሪያው ሰው በሰጠው የድኅነት ተስፋ መሠረት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ስለ ሰው ልጅ ሲል የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ ለማስታወስ መስቀልን እናከብራለን ለመስቀልም እንሰግዳለን ።

መስቀል በአዳኝነቱና በፈዋሽነቱ ላመነበት ሰው ሁሉ ጽኑ ኃይልና ብርታት ያለው ጸጋ ነው መስቀል ለክርስቲያኖች መመኪያና የሕይወትም መታወቂያ ነው። መስቀል የላዕላዊ ዓለም የነጻነት ዓርማና የክርስቲያንነታችን መንፈሳዊ ምልክት ነው ።

፩ኛ/ መስቀል ላመነበት ሰው ሁሉ ኃይልና ጽንዕ መሆኑን ሲገልጽ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ፡ የመስቀሉ ቃል (ነገር) ለሚጠፉት ሞኝነት ሲሆን ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው ብሏል ፩ኛ ቆሮ. ፩/፲፰

ከዚህም የተነሣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መስቀል ኃይላችን ነው መስቀል ጽናታችን ነው እያለች ትጸልያለች ። ታስተምራለች።

፪ኛ/ መስቀል የክርስቲያን መመኪያ መሆኑንና ያለ መስቀል መመኪት እንደማያስፈልግ ከላይ የተጠቀሰው ሐዋርያ ሲያስረዳ “ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ ሲል ተናግሮአል ገላ ፮፡፲፬ ይህ ቃል የሚያመለክተውና ክርስቲያኖችን የሚያስገነዝበው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በአዳኝነቱ ለሚያምነው ሁሉ ጽኑ አምባ ኃይልና መከታ መሆኑን ነው።

፫ኛ/ መታወቂያና የሕይወት አርማ መሆኑ በብዙ ምሳሌና አርአያ በተለያዩ ቅርጾችም በክርስቲያኖች ቤት ይታያል ይኸውም በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ የተሰኙ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ከመውደዳቸው የተነሣና ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ በማስታወስ በልብሳቸው በግንባራቸው ሴቶችም በቀሚሳቸው ሁሉ መስቀልን እያደረጉና የመስቀልን ቅርጽ እያስጠለፉ የክርስቲያንነታቸው መታወቂያ አድርገውት ይገኛሉ በዚህም መልክ የሚታዩት ክርስቲያኖች በጥቂቱ የሚገመቱ አይደሉም ።

የክርስቶስን አዳኝነት እያሰቡና እያስታወሱ መስቀልን የሚይዙና ለመስቀል የሚሰግዱ መንፈሳዊ ክብር አላቸው ።

የመስቀል አዳኝነትና ፈዋሽነትም የሚታወቀው በክርስቲያናዊ ዓለም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከክርስቲያናዊ እምነት ውጭ በሆኑ ሰዎች የጤና ባለሞያዎችም ጭምር የታወቀ ነው ለማለት እንችላለን ፡ ለምሳሌ በዓለም ሁሉ ያሉ ሆስፒታሎችና በመላ ዓለም የሚገኙት የጤና ባለሞያዎች የሆስፒታሉም ሆነ የአምቡላንስ ዓርማ ቀይ መስቀል ነውና ከዚህ የበለጠ የድኅነት አርማና ከዚህ የተሻለ እውነተኛ ምስክር ሌላ አናገኝም ።

ታዲያ በመላ ዓለም ያሉት የሕክምና ባለሞያዎች ክሊኒኮችና የመድኃኒት ቤቶች ዓርማቸውና ምልክታቸው መስቀል ሁኖ መታየቱ የመስቀልን አዳኝነት የሚያመለክት ነው እንላለን ። ከዚህ ላይ ሳንጠቅሰውና ለአንባብያን ሳናስገነዝበው ማለፍ የማይገባን ነገር ቢኖር መስቀል መድኃኒታችን ነው መመኪያችንና መታወቂያችንም ነው ብለን መስቀልን ስናከብረው ያለ ምክንያት አይደለም መስቀልን የምናከብረውና ለመስቀል የምንሰግደው የክርስቶስ ቅዱስ ደም ስለፈሰሰበትና አምላካችን ክርስቶስ በደሙ ስለ ቀደሰው ነው እንጂ እንጨቱን ለማምለክ ወይም እንጨቱን በአምላካዊ ደረጃ በመመልከት እንዳይደለ መገንዘብ ያስፈልጋል ።

እንደሚታወቀው አምላካችን ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ እንደዚሁም ቅዱስ ደሙን አፍሶ ሳይቀድሰው መስቀል የመርገም እንጨትና የወንጀለኞች መቅጫ እንደ ነበረ በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግቦ የሚገኝ ነው ።

ከልደተ ክርስቶስ በፊት የነበሩት አንዳንድ ኅብረተሰብ ከመካከላቸው ለሞት የሚያበቃውን ወንጀል ሠርቶ የተገኘ ሰው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ይሞት እንደ ነበረ ሙሴ በጻፈው ዳግም ሕግ



www.ethiopianorthodox.org

ወይም በአራት ዘጻግም እንዲህ ይላል "ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢአት ቢሠራ እንዲሞትም ቢፈረድበት በእንጨት ላይም ብትሰቅለው በእንጨት ላይ የተሰቀለ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነው" ይላል ዘጻግ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

ስለዚህ መስቀል ከልደተ ክርስቶስ በፊት የመርገምና የወንጀለኞች መቅጫ እንደ ነበር በዚህ ይታወቃል ።

ባሁኑ ጊዜ ግን ያ የወንጀለኞች መቅጫ የነበረው መስቀል ክርስቶስ ስለ ቀደሰው የወንጀለኞች ፈውስ የአጋንንት ወር ሁኖ ይገኛል ።

እኛም ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ትምህርት እንመክበታለን በክርስቲያንነታችን እንኮራበታለን ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም በመስቀል ላይ ተሰቅለህ መንፈሳዊ ነጻነታችንን አጐናጸፍከን ተወስዶብን የነበረውንም ልጅነት በመስቀል ላይ በተቀበልከው መከራ መለስክልን እያልን እንሰግድለታለን ይኸውም ነቢዩ ዳዊት (ወንሰግድ ውስተ መካነ ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ) እግሩ በቆመበት እንሰግዳለን ያለውን መሠረት በማድረግ ነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እግር በቆመበት ማለትም ቀራንዮ ሲሆን ቀራንዮ ማለትም ትርጉሙ መስቀል ማለት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል ።

ይህም መስከረም ፲፯ ቀን በየዓመቱ ሲከበር የሚኖረው የመስቀል በዓል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር መስቀል ለብዙ ዘመናት ተቀብሮ ኖሮ በንግሥት እሌኒ አማካይነት መጋቢት ፲ ቀን የተገኘ ሲሆን ንግሥት እሌኒ ካገኘችው በኋላ በመስቀሉ ስም ቤተ ክርስቲያንን አሳንፃ ያስቀደሰችበት የመስቀል ቅዳሴ ቤቱ በመሆኑ እነሆ ሲከበር ቆይቷል ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል መስቀልንም ማክበራችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወሳችንና ማክበራችን ነው የመስቀሉ ነገር ለሚያምኑት ኃይል ነው ለሚጠፉት ግን ሞኝነት ነው ተብሎ እንደ ተጻፈ ለኛ ለምናምን ኃይሉን ይስጠን ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ

# የግሸን ማርያም ታሪክ በአጭሩ

የግሸን ማርያም ደብር ጥንተ ታሪክ እንደዚህ ነው ፡ ይህች ታላቅ ደብር የምትገኘው ወሎ ሀ/ስብከት አንባሰል አውራጃ ሲሆን አዋሳኞቿ መቅደላና በሽሎ የጁና ደላንታ ናቸው ፡

ወደግሸን ዓንባ ለመሔድ በረሐ አቋርጦ በሽሎን በመሻገር የሶስት ሰዓት መንገድ አቀበት በመውጣት አንድ ቀን ተኩል ሙሉ ተጉዞ ነው ፡

የዓንባው በር አንድ ሁኖ ዙሪያውን በገደል የተከበበች ናት ልክ ጥበበኛ ሰው አስቦ ተጨንቆ ከቋጥኝ ድንጋይ በመክፈል እንደሞሰብና ጠረጴዛ በማድረግ በመስቀለኛ ያነጿት ትመስላለች ። በዚህችም ታሪካዊት ቦታ ላይ ዓፄ ካሌብ ወደ ሀገረ ናግራን ዘምተው የአሕዛብን ንጉሥ ፊንሐስን ድል አድርገው ሰማዕታተ ናግራንን አስቀብረው በሕይወት ያሉትን አቋቁመው ሲመለሱ ታቦተ እግዚአብሔር አብን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ በግሸን ዓንባ ላይ ቤተ መቅደስ ሠርተው ቀያሽና አዳሽ መድበው ደብረው ታል፡ ከዚያም በ፲፩ኛው መቶ ዘመን ላይ ንጉሥ ላሊበላ የግሸንን ዓንባ ለማየት ከቦታው ድረስ ሂዶ ዓፄ ካሌብ የተከሉትን የእግዚአብሔር አብን ቤተ መቅደስ ያገኛል ከዚያም የቦታዋን ማማር የዓንባውን ስፋትና ዙሪያዋን በገደል መከበብ ተመልክቶ ደስ ስለአለው የቋጥኝ ቤተ መቅደስ ሠርቶ የእግዚአብሔር አብን ታቦት ለማስገባት ሁለት ክፍልና ሁለት ዓምድ (ምሰሶ) ሠርቶ ሲፈጽም በሕልሙ ወዳጄ ላሊበላ ሆይ በዚህ ላይ ቤተ መቅደስ የሚሠራልኝ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ነው እንጂ አንተ አይደለህም ያንተ ክፍል በሌላ አውራጃዎች ነው ብሎ ስለ አዘዘው አቋርጦ ወደ መናገሻ ከተማው ተመልሷል ።

ከዚህ በኋላ ለነጋሢ ዘሮች ለሆኑ ለመሣፍንቶችና ለመኳንንቶች የግዞት ቦታ ሆኖ ኑሯል ብዙ የነጋሢ ዘሮችም የብሉያትንና የሐዲሳትን የታሪክ መጻሕፍቶችን ተመርውበታል ፡ በታቦተ እግዚአብሔር አብም ተማኅፅኖ በማድረግ ብዙ ምሥጢር ተገልጾላቸዋል ።

በኋላም በ14ኛው መቶ ዘመን ላይ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ የክርስቶስን ግማደ መስቀሉን ከእግዚአብሔር አብ ታቦት ጋር በመቀላቀል ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ደብሩ ርስተ ጉልት ሰጥተው ደብሩን አደስውታል ።

የክርስቶስ ግማደ መስቀሉም በግሸን ዓንባ ላይ መጥቶ ተቀምጧል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ በዕፀ መስቀል በሰቀሉት ጊዜ ከመከራው ጽናት የተነሣ ደሙ ወርዶ የተሰቀለበትን መስቀል አልብሶት ስለነበረ ፡ ከሞተ በኋላ ከመስቀሉ አውርደው ቀብረውት በ፫ኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ነገር ግን ተሰቅሎበት የነበረው የእንጨት መስቀል እንደ ፀሐይ እያበራ አጋንንትን ሲያስወጣ የታመመ ሲፈውስ ሙታንን ሲያስነሣ አይሁድ ቀንተው ጉድጓድ ቆፍረው ከቀበሩት በኋላ የቤት ጥራጊና አመድ እንዲያርፍበትና የቆሻሻ መከማቻ እንዲሆን አደረጉ ከዚያ ዘመን ጀምሮ ከ፱፻ ዘመን በላይ የተከማቸው ቆሻሻ እንደ ተራራ ሆነ ከዚህ በኋላ የታላቁ ቆስጠንጢኖስ እናት እሌኒ ንግሥት የክርስቶስን መስቀል ቆፍራ ለማውጣትና በክብር ቤተ መቅደስ አሠርታ ለማስቀመጥ መስከረም 17 ቀን በዕጣን ጢስ ምልክት ቁፋሮ አስጀምራ በመጋቢት ወር አግኝታ በማውጣት ታላቅ ቤተ መቅደስ ነልንታ ላይ አሠርታ በክብር አስቀመጠችው ይህም መስቀል እንደ ዕንቁ እና ፀሐይ እያበራ ድውይ እየፈወሰ አጋንንትን እያስወጣ ሙት እየሥነሣ ዕውር እያበራ ተአምራቱን በልዩ ልዩ መንገድ ይገልጽ ጀመረ የመስቀሉም ታላቅነት በመላ ዓለም ስለታወቀ የፋርስ ንጉሥ መስቀሉን ማርኮ ፋርስ ወስዶ አስቀመጠው በዚህ ጊዜ የኢየሩሳሌም ምእመናን የሮማን ንጉሥ ሕርቃልን ዕርዳታ በመጠየቅ እንዲመለስ አድርገው በኢየሩሳሌም ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ ኃያላን ነገሥታት ይህን መስቀል እኔ እወስድ እኔ እወስድ እያሉ ጦርነት ፈጠሩ ፡

በዚህ ጊዜ የኢየሩሳሌም የቁስጥንጥንያ የአንጾኪያ የኤፌሶን የአርማንያ የግሪክ የእስክንድርያ የመሳሰሉት የሃይማኖት መሪዎች ስላማዊ ስልፍ አድርገው ጠቡ የሚበርድበትን ዘዴ ፈልገው ክርስቶስ ተሰቅሎበት የነበረውን መስቀል ከአራት (4) ክፍለው በዕጣ ተከፋፍለው በየሀገራቸው ወስደው አስቀመጡት የቀኝ እጁ ያረፈበት ግን የደረሰው ለአፍሪቃ ስለነበረ በግብፅ የሚገኘው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ተረክቦ ወስዶ በክብር በማርቆስ ቤተ መቅደስ ውስጥ አስቀመጠው ይህ ግማደ መስቀልም ለብዙ ዘመናት በእስክንድርያ ሲኖር ሳለ በኢትዮጵያ ረኀብና በሽታ ድርቅ ሆነ ይህም ከባድ ጉዳት የተከሰተው በዳግማዊ ዓፄ ዳዊት ዘመን መንግሥት ነበር ፡ በዚህም ችግር ዓፄ ዳዊት አዝነው ምናልባት ይህ ከፍተኛ ችግር ቢወገድልኝ ብለው ወደ እስክንድርያ እንዲህ የሚል መልእክት ላኩ ።

የእስክንድርያ ፓትርያርክ አባ ገብርኤል ሆይ በሀገሬ በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ የሆነ ረሀብና ልዩ ልዩ በሽታ ድርቅ ስለሆነብኝ የክርስቶስ ግማደ መስቀል እንዲላክልኝ በትህትና አሳስባለሁ ፡ ምክንያቱም ይህ መስቀል ለመላ አፍሪካውያን ስለሆነ ኢትዮጵያም በአፍሪካ ውስጥ ስለሆነች የኢትዮጵያ ውያን ችግር የአፍሪካ መሆኑን አስታውሼ ነውና በደብዳቤ ጥያቄ የላክሁት ጥያቄዬ ተቀባይ ይኖረዋል ብዬ በተስፋ እጠባበቃለሁ (ዳግማዊ) ዓፄ ዳዊት ይህ መልእክትም ለእስክንድርያው ፓትርያርክ ለአባ ገብርኤል በደረሰው ጊዜ ከሊቃነ ጳጳሱና ኤጲስ ቆጶሳቱ ጋር መክረው የኢትዮጵያ ችግር የእስክንድርያ ችግር ነው ።

ኢትዮጵያ እስክንድርያ ናት እስክንድርያ ኢትዮጵያ ናት ስለ ዚህ የንጉሡ የዓፄ ዳዊት ጥያቄ አግባብ ስለሆነ ይህን ግማደ መስቀል እንላክላቸው በሚል ውሳኔ የክርስቶስ ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ ተልኮ አስዋን ድረስ ዳግማዊ ዓፄ ዳዊት ሔደው በእግራቸው እያሸበሸቡ በእጃቸው እያጨበጨቡ በግንባራቸው እየሰገዱ መስከረም 10 ቀን በደስታ ተቀብለው ስናር ሲደርሱ ዳግማዊ ዓፄ ዳዊት በድንገት ስለአረፉ (ስለሞቱ) መስቀሉ በዚያው ቆይቷል። ልጃቸው ዘርአ ያዕቆብ በነገሡ ጊዜ ጌታ ተገልጾ ወዳጄ ዘርአ ያዕቆብ ሆይ አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል መስቀሌን በመስቀልኛ ቦታ ላይ አስቀምጥ የሚል ምሥጢር በተደጋጋሚ ስለ ተገለጸላቸው በ14ኛው መቶ ዘመን ላይ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ወደስናር ሔደው የክርስቶስን ግማደ መስቀል በብዙ ካህናትና ሠራዊት አሳጅበው ወደ መካከለኛዋ ኢትዮጵያ ምድር ላይ ደርሰው በመጀመሪያ ደብረ በርሃን ላይ መቅደስ ሠርተው ለማስቀመጥ አስበው ሳለ መሬቱ እየተንቀጠቀጠ ከመታየቱም በላይ አንብር ለመስቀልየ በዲበ መስቀል መስቀሉን በመስቀለኛ ቦታ ላይ አስቀምጥ የሚል ቃል ከሰማይ መጣላቸው ከዚህ በኋላ መስቀለኛ ቦታ በመፈለግ ከብዙ ቦታ ላይ መስቀሉን አሳርፈውት ነበር ለምሳሌ በሸዋ በመናገሻ ማርያም በወጨጫ በጉንደ መስቀል በወሎ በገነተ ልዑል በጫጫ መስቀል ከመሳሰሉት አሳርፈውት እንደነበር ይተረካል ።

ነገር ግን እነዚህ ቦታዎች ለግማደ መስቀሉ መኖሪያ ለመሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለአልተፈቀደ መሬቱ ሲንቀጠቀጥ ታይቷል ። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ሰባት ቀን ሱባዔ ቢያደርጉ ቦታ



www.ethiopianorthodox.org

ውን የሚመራቸው ዓምደ ብርሃን መጥቶ ከፊታቸው ቆመላቸው በዚያ በዓምደ ብርሃን መሪነት ግሸን ዓንባ ሲደርሱ ዓምደ ብርሃኑ ከፊታቸው እንደቆመ ተሠወራቸው ፡ ቦታውም ለመስቀሉ መኖሪያ ለመሆኑ ምልክቱ መሬቱ እንደሌላዎቹ ቦታዎች ሲንቀጠቀጥ አልታየም ፡

ንጉሡ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብም የዓንባውን ሜዳ ዙሪያውን ተመልክተው እውነትም ይህ ቦታ ለመስቀሉ የሚገባ ነው ምክንያቱም መስቀሉን በመስቀለኛ ቦታ አስቀምጥ እንደተባልኩ መስቀለኛ ዓንባ መሆኑን ዙሬ ተመለከትኩት ብለዋል ። በዚህም ዓንባ ላይ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ለመስቀሉ መኖሪያ ከመቅደሱ ውስጥ ምስዋር የሆነ ዋሻ በማስቆፈር በዚያ በክብር ካስቀመጡት በኋላ በላዩ ላይ በዓፄ ካሌብ ዘመን የተተከለውን የእግዚአብሔር አብን ታቦት በማስገባት ቅዳሴና ውዳሴ እንዲደረግበት ብዙ ካህናትና መዘምራን ተክለውበታል ።

ለካህናቱና ለታቦቱ ማደሪያም ብዙ ርስት ጉልት ብዙ ንዋየ ቅድሳት ሰጥተው የጥንቱን ደብርነት አጽንተው ብዙ ሥርዓት ሠርተው ደንብም ወስነውበታል ።

ከዚህ ሌላ ከሐዋርያትና ከሰማዕታት ከጻድቃንና ከሊቃነ ጳጳሳት ከቅዱሳት አንስት አጽም ከግማደ መስቀሉ ጋር እንዲቀመጥ አድርገዋል ፡ በተጨማሪም ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ለብሶት የነበረው ቀይ ልብስ ፡ ከሮም የመጣው ከለሜዳው ፡

ከአፍርንጊ ሀገር የመጣው ሐሞት የጠጣበት ሰፍነግ ፡ የሐንስ የግለው የኩርዓተ ርእሱ ሥዕል ፡ ሉቃስ የሣላቸው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ሥዕሎች ይገኙበታል ። ከእግዚአብሔር አብ ቤተ መቅደስ አጠገብ ደግሞ የዓፄ ዘርአ ያዕቆብ እኅት እሌኒ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ስም ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠርታ ጥር ፳፩ ቀን ቅዳሴ ቤቷን አክብራለች ።

አስቀድመን እንደገለጽነው ዓፄ ዘርአ ያዕቆብም በመጀመሪያ ግማደ መስቀሉን ከስናር ያመጡት መስከረም ፳፩ ቀን ነው ከዚያም ወደ መካከለኛው ኢትዮጵያ ምድር ያደረሱበት መስከረም ፳፩ ቀን ሲሆን ፡ በግሸን ዓንባ ደግሞ መስከረም ፳፩ ቀን አስገብተው ቅዳሴ ቤቱን ያስከበሩትም መስከረም ፳፩ ቀን ነው ፡ በዚህም ምክንያት መስከረም ፳፩ ቀን በየ ዓመቱ በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት ይከበራል ።

ከዚህ በላይ በተገለጹት ቀኖች የቅዳሴ ቤቱን አከባበር ባርከውና ቀድሰው ያቀረቡት ሊቃነ ጳጳሳት አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል የተባሉ በዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን የነበሩ የኢትዮጵያ ጳጳሳት ናቸው በመጨረሻም ንጉሡ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ጳጳሳቱ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ለስባት ቀናት ሱባዔ በማድረግ ከእግዚአብሔር ዘንድ በጸሎት ተገናኝተዋል ጌታም ተገልጾ ወዳጄ ዘርአ ያዕቆብ ሆይ ወዳጆቼ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ሆይ ይህች ቦታ እኔ ተወልጄ ያደኩባትን ቤተ ልሔምንና ናዝሬትን ገሊላን ትሁን ፡ የተሰቀልኩባትን ቀራንዮን ትሁን ፡ የተቀበርኩበትን ጎልጎታን ትሁን ፡ በዚችም ቦታ የተማፀኑትን ሁሉ ቸርነቱ ትጉበኛቸዋለች ጠለ ምህረቴንም ከቦታዋ አልለይባትም ሲል የምሕረት ቃል ኪዳን ሰጥቶባታል ። ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ታሪክ የተገኘው ጤፉት ከሚባል መጽሐፍ ነው ይህ ጤፉት የሚባለውም መጽሐፍ በዚሁ በግሸን እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል ።

እንባብያን ሆይ እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተረዳችሁት ወደዚች ታሪካዊት ቦታ እየሔዱ መማፀንና መጸለይ አስፈላጊ ስለሆነ ቢቻል በዓመት ፫ ጊዜ ባይቻል በየዓመቱ መስከረም ፳፩ ቀን እየሔዱ ጸሎት ማድረስና መማፀን ይገባል እንላለን በመንገድም በኩል ግሸን ከዓንባው ሥር ድረስ መኪና ስለሚገኝ ችግር የለም በእግርም ቢኬድ ከደሴ ተነሥቶ በአንድ ቀን ተኩል ይደረሳል ከዚያም ከዓንባው ከተገባ በኋላ የውሃ የምግብና የማገዶ ችግር በፍጹም የለም ። የግሸን በሩ አንድ ስለሆነ በቀላሉ ሌባና ወንበዴ ሊያጠቃው አይችልም አየሩም ቀዝቃዛ ስለሆነ ለጤና ተስማሚ ነው ፡

የግሸን ማርያም ደብር በፊት ደብረ እግዚአብሔር አብ ከዚያም ደብረ ነጐድጓድ በ፫ኛው ጊዜ ደብረ ከርቤ ትባላለች በግሼን ዓንባ ውስጥ የግሼን ተወላጅ የሆኑ የጐንደር ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በ፲፱፻፶፬ ዓ. ም ላይ የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት ከኢየሩሳሌም አምጥተው ቤተ መቅደስ አሠርተው ቅዳሴ እንዲቀደስበት አድርገው እስከ አሁን ይቀደስበታል ይወደስበታል ።

በግሸን ዓንባ ከሁለት ቦታ ላይ በክረምት ዝናብ ክምችት ሁለት ባሕር ይገኛል ፡ አንዱ የሕዝብ የዘወትር መጠጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለመጠመቂያ በጸበልነት የሚያገለግል ነው በንዋየ ቅድሳት በኩል ደግሞ የብሉያትና የሐዲሳት ሊቃውንትና ገድለ ቅዱሳት መጻሕፍት የወርቅና የብር አልባሳትና መስቀሎች ዘውድና አክሊል ከበሮና ጽናጽል መቋሚያ በብዛት ይገኛል እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደዘረዘርንላችሁ ለታሪክም ለምንፈሳዊ ዓለምም ቦታ ስለሆነች የግሸን ማርያምን ደብር እንጐብኛት በክብርም እንጠብቃት እንላለን ።

የታሪኩ አቅራቢ አባ ገብረ መስቀል ተሰፋዬ
ዘገነተ ማርያም



# ዘመነ ጽጌ

ዘመነ ጽጌ ተብሎ የሚጠራው በቤተ ክርስቲያናችን ሕግና ሥርዓት ከመስከረም ፳፮ ኅዳር ፮ ቀን ያለው ጊዜ ነው ፡ ይህ ወቅት ዘመነ ክረምት አልፎ ወርኃ መጸው የሚተካበት ጊዜ በመሆኑ ከየፍርኩታው የጠራ ውኃ የሚፈልቅበት ፡ ምድር በሥነ ጽጌያት የምታሸበርቅበት ፡ ልዩ ልዩ አዝርዕት ዘርዝረው ፡ ዕፅዋት በልምላሜ አጊጠው ፍጥረታትን የሚያስደስቱበት ፡ ንጹሕ አየር የሚነፍስበት ፡ ሰማይ ብርሃን ተጐናጽፎ የሚታይበት በመሆን ለሰው ልጆች ልዩ ስሜትና አድናቆትን ያሳድሩባቸዋል ።

ከላይ ከተጠቀሱት የዘመነ ጽጌ ሳምንታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በዕለተ ሰንበታት ከየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ የዓመቱን ቃለ እግዚአብሔር ሲያደርሱ ያድራሉ ። የዚሁ መንፈሳዊ አገልግሎት ዋና ዓላማም የእመቤታችን ዘመነ ስደት ለማዘከር ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን አበው መምህራንና ሊቃውንት ደንግገው ባስተላለፉት መሠረት ለመፈጸም ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር በዘመነ ስደቱ ወደ ምድረ ግብፅ ሲወርዱ ኢትዮጵያ ሀገራችንን በትእምርተ መስቀል ሲባርኳት እመቤታችን አይታ ይህች አዘውትረህ የምትባርካት አገር ማን ትባላለች? ብላ ጠየቀችው ጌታችንም ኢትዮጵያ ትባላለች አላት እንግዲያስ ይህች አገር ለኔ አስራት በኩራት ትሆነኝ ዘንድ ስጠኝ አለችው ፡ እርሱም በማይታበል ቃሉ ክብርት እናቱ ሆይ ፈቅጀልሻለሁ ፡ ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳይ የምትለምኝ ውንም ሁሉ እፈጽምልሽ ዘንድ ቃል ገብቼልሻለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶላታል ።

በዚህም ምክንያት ከጥንት ጀምሮ የእመቤታችን ፍቅር በአባቶቻችን ፍቅር እጅግ የተወደደና የጸና ሆኖ ኖሮአል ። ከዚሁ ጽኑ ፍቅራቸው የተነሣ ይህ የስደትዋ ዘመን ከሌሎቹ ክርስቲያኖች ይልቅ በተለየና ከፍተኛ በሆነ የፍቅር ስሜት ሲያከብሩት ኑረዋል ። ይህ የተቀደሰ ተግባር ከአባቶቹ በትውፊት የተረከበው የዘመኑ ትውልድም ከእመቤታችን ጋር ያለውን ጽኑ ፍቅር በዘመነ ስደቷና በየዓመቱ በሚያሳየው የተቀደሰ ትሩፋትና በሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት የቱን ያህል እንደሆነ ለመረዳት ያስችለናል ።

በማቴዎስ ወንጌል እንደምናነበው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን ኢየሱስን በቤተ ልሔም እንደወለደችው ጥቂት ወራት ቆይቶ ሰብአ ሰገል ወደሄሮድስ መጡ ፡ የአይሁድ ንጉሥ የተወለደው የት ነው? ሲሉም ጠየቁት በዚያን ጊዜ ሄሮድስ እጅግ ደነገጠ ኢየሩሳሌምም ም ከእርሱ ጋር ፡ ሄሮድስ ሊቃውንቱን ጠርቶ የአይሁድ ንጉሥ የሚወለደው የት ነው? ብሎ ጠየቃቸው እነርሱም በቤተልሔም ነው አሉት ። ሄሮድስም ሰብአ ሰገልን ወደቤተልሔም ሂዱ ። ባገኛችሁትም ጊዜ መጥታችሁ ንገሩኝ እኔም ሄጄ እስግድለታለሁ አላቸው እነርሱ ግን ጌታችንን ካገኙት በኋላ ለአምላክነቱ የተገባ ስግደትንና ስጦታንም አድርገውለት በመልአኩ እምርታ መሠረት በሌላ መንገድ ወደሀገራቸው ሄዱ። ሄሮድስ ግን ሰብአ ሰገል እንደተሳለቁበት ባየ ጊዜ በኢየሩሳሌምና በቤተ ልሔም ዙሪያ የነበሩትን ሕፃናት ሁሉ ልብስና ተለብ እስጣቸዋለሁና ሰብስቡልኝ ሲል በጉባሉት (በተንኰል) አዋጅ አስነገረ። በዚሁ ወቅት የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ዮሴፍን በሕልም "ተነሥ ሕፃኑን ሄሮድስ ሊገድለው ይፈልገዋልና ከእናቱ ጋር ይዘኸው ወደ ግብፅ ሽሽ" ሲል ነገረው ።

ቅዱስ ዮሴፍም መልአኩ በሕልም በነገረው መሠረት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከልጅዋ ከወዳጅዋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አገልጋዩ ሰሎሚንም ይዞ ወደ ምድረ ግብፅ ተነሣ ፡ ከኢየሩሳሌም (ከቤተልሔም) ወደ ምድረ ግብፅ ተሰደ (ማቴ ፪፡፲፫ ፲፰) ።

ሄሮድስ ግን ሰብአ ሰገል እንደ ተሳለቁበት ባየ ጊዜ በቤተልሔምና በአውራጃዎችዋ ያሉትን ሁለት ዓመት የሆናቸውና ከዚያም ያነሱትን ሕፃናት ሁሉ ሰብስቦ በሰይፍ ስለት ፈጅቶአቸዋል። ሕፃናቱን እንደበግ አርዶአቸዋል እንደጐመን ቀርድዶአቸዋል ደማቸውም እንደክረምት ውኃ ጐርፎ አል ።

እመቤታችን ፡ ጌታችንና ቅዱስ ዮሴፍ ሰሎሜ ወደ ግብፅ ሲሸሹ



www.ethiopianorthodox.org

የቀኑ ሐሩር የሌሊቱ ቁር እጅግ አስቃይቶአቸዋል ፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከቤቷ ወጥታ መከራም አይታ የማታውቅ ስትሆን በዚህ ወራት ግን እንደ ፀሐይ የሚያበራ ፊቷ ጠወለገ ፡ እንደ ጨርቅ የለሰለሰ እግርዋ በእሾዋ ረመጥ ተቃጠለ በውኃ ጥም ከንፈርዋ ደረቀ ፡ እም ይህን በሦስት ዓመቷ ከናት ከአባትዋ ተለይታ በቤተ መቅደስ ገብታ በመጋረጃ ተሸጋታ ከመኖርዋም በላይ አባ ሕርያቆስ በመጽሐፈ ቅዳሴው "ድንግል ሆይ ምድራዊ ኀብስትን የተመገብሽ አይደለሽም ፡ ከሰማየ ሰማያት የበሰለ ሰማያዊ ኀብስትን ነው እንጂ ፡ ድንግል ሆይ ምድራዊ መጠጥን የጠጣሽ አይደለሽም ከሰማየ ሰማያት የተቀዳ ሰማያዊ መጠጥን ነው እንጂ ብሎ ያወደሳት በልጅነት ኀብስት ሰማያዊ ዕዋዕ ሰማያዊ ስትሲሰይ (ስትመገብ) የኖረች እመቤት ፡ የዛፍ ጥላ የድንጋይ ከለላ በሌለበት በዚያ ምድረ በዳ እንደረመጥ የሚመሸልቀው እሾዋ ያንን ዕንቡጥ እግሯን እያቃጠለ ሲፈጃት ያየ ርኅሩኅ ሲያዝንላት እምነት የሌለው አረመኔና ጨካኝ ደግሞ ሲቀልድባት ትዕግሥት ልማድዋ ነውና በትዕግሥት ትጓዝ ነበረች ።

ስለዚህም ይህ አባ ሕርያቆስ የሚባል የቤ ክርስቲያን አባት አሁንም የእመቤታችንን የመከራ ዘመን በማስታወስ "ድንግል ሆይ ርጉም በሆነው በሄሮድስ ዘመን ከልጅሽ ከክርስቶስ ጋር ካገር ወደ ገር ስትሸሺ ካንቺ ጋር መሰደዱን አሳስቢ ፡ ድንግል ሆይ ከዐይናችሽ የፈሰሰውንና በተወደደው ልጅሽ ፊት የወረደውን መሪር ዕንባ አሳስቢ ፡ ድንግል ሆይ ረኀቡን ጥሙን ችግሩንና ኀዘኑን ከእርሱ ጋራ የደረሰብሽንም ጭንቀ ሁሉ አሳስቢ ሲል ይማለዳል ።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም በመጽሐፈ ድጓው "ዕዝነ ልቡና ያለው ሰው መከራሽንና ስደትሽን አስቦ ያልቅስ" ብሎ አል ። አዎ በዚህ ዘመን የስደትዋ ወራት እፍኝ ጥሬ ቆርጥመው ጥርኝ ውኃ ተጎንጭተው የመከራዋን ዘመን እያስታወሱ በኀዘንና በዕንባ ንስሐ እያለቀሱ በረከትዋን ረድኤትዋን የሚሳተፉ ቅዱሳን ኢትዮጵያውያን ብዙዎች ናቸው ።

እነ ቅዱስ ያሬድ እነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እመቤታችንን በጽጌ የመሰሏታል ጽጌ የማይጠገብ ነው ጽጌ አስደሳች ነው አእምሮን ያድሳል ልዩ ስሜት ይሰጣል ሥፍራ (ቦታ) ያደምቃል ። ያሸበርቃል መልኩ ያስጐመጃል ፡ ለመሆኑ በጽጌይት የማይደሰት ምን ዓይነት ፍጡር ይገኛል? በጽጌይት ፍሬያት ምድር ይገኛሉ በፍሬያት ምድርም ፍጥረታት ከረሀብ ከጉስቁልና ከሞትና ከጥፋት ይድናሉ ስለዚህ የእመቤታችን በጽጌ መመሰል ትክክለኛ ትርጉምን የያዘ ነው ይኸውም እመቤታችን በመልኳ ፡ በውበትዋ ፡ በደም ግባትዋ ፡ በንጽሕናዋ የማትጠገብ አበባ ነች ። ከእርስዋ የተገኘው ፡ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሙቶ ተነሥቶ እኛን ከዘለዓለማዊ ሞት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ያሸጋገረን ፡ ከሞተ ሥጋና ከሞተ ነፍስም ያዳነን ልጅዋ ወዳጅዋ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የሕይወት ፍሬ ነውና ።

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ውዳሴና ቅዳሴ በዚህ ዘመን ጽጌ በየገዳማቱና በየአድባራቱ ሲደረስ የሚያድሩ በስሟ የተደረሱ መጻሕፍት እጅግ ብዙ ናቸው የስደቷን መከራ የሚናገረው ማኅሌተ ጽጌ የተባለ መጽሐፍ በማኅሌት ሊቃውንቱ ሲያመረግዱት ፡ ሲያሸበሽቡት ያድራሉ በቅዳሴ ጊዜም በስሟ አባ ሕርያቆስ የደረሰላትን መጽሐፈ ቅዳሴ እንበለ አጽርኦ ይቀደሳል በዚህ የተቀደሰ አገልግሎት የሚሳተፉ ሁሉም መንፈሳዊ ሕይወታቸው ይለመልማል የስደትዋን ምሥጢር ጠለቅና ረቀቅ ባለ ሁኔታ የሚመረምሩትም በኀዘንና በልቅሶ ዓይነ ልቡናቸውን ከፍተው ወደ እመቤታችን ሲያንጋጥጡ ያድራሉ ይውላሉ ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጅዋ ከወዳጅዋ ጋር የተቀበለችው የመከራና የስደት ዘመን እንዲህ በቃል ስንናገረው ፡ በመጽሐፍ ስናነበው ቀላል ይመስለን ይሆናል ። ነገር ግን እጅግ በጣም ከባድና አስቃቂ እንደሆነ የስደትን መከራ የቀመሰ ሁሉ ያውቀዋል ስደት ከተወለዱበት ቀየ ፡ አፈር ሲፈጩ ፡ ውኃ ሲራጩ ካደጉበት መንደር ፡ ከወዳጅ ከዘመድ ሲጨዋወቱበት ከነበረው ሥፍራ ሲፈልሱ ከተዳሩበት ፡ ከተኳሉበት አካባቢ ተለይቶ ወደ ማያውቁት ወደማያውቃቸው አገር ተንከራ (ፈልሶ) መንከራተት መተላለፍ ከቶ እንዴት ያስቃያል ?

ስለዚህ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሕፃኑን ይዛ በረሀ ለበረሀ የተንከራተተችው በሌላው መልኩ ሁላችንም መከራ፡ ችግር ፡ ፈተና ሲደርስብን በትዕግሥት እንድንቀበለው ፡ እንዳናማርር ፡ በፈተና ተሸንፈን እንዳንወድቅ ሃይማኖታችንንም እንዳንክድ ከአምላካችን እንዳንጣላና እንዳንርቅ እርስዋን አብነት አድርገን እንድንታገሥ ነው ። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ለራሱ በሌላም ላይ ፈተና እንዳይደርስበት ለማድረግ ሥልጣኑ የባሕርዩ ሲሆን ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር መከራ ስደተን በፈቃዱ መቀበሉ ለኛ አርአያና ምሳሌ ለመሆን ነውና የእናትና ልጁን መከራና ስደት አብነት አድርገን የሚመጣብንን በትዕግሥት ድል አድርገን የማያልፈውን የሕይወት አክሊል ለመቀዳጀት እንችል ዘንድ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በረከትና ረድኤት አይለየን ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በኃይሉ በቸርነቱና በጸጋው ያጽናን ።

ሊቀ ትጉሃን ገ/ክርስቶስ ኃ/ማርያም



# ዜና ሊቃውንት

## የታላቁ ሊቅ የሊቀ መራህያን ይትባረክ ገብረ ሚካኤል አጭር የሕይወት ታሪክ ።

ሊቀ መራህያን ይትባረክ ገ/ ሚካኤል በትግራይ ሀ/ስብከት በአክሱም አውራጃ ልዩ መጠሪያ ስምዋ ማኅበረ ጻድቃን ደጓ በምትባል መንደር ከአባታቸው ከመምህር ገ/ሚካኤል ገ/ሕይወት ከእናታቸው ከወይዘሮ አበራሽ ገብረ ሥላሴ ጥር ፳፯ ቀን ፲፰፻፹፱ ዓ/ም ተወለዱ ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በትውልድ ሀገራቸው ከመምህር ገ/ሥላሴ ሣህሌ ፊደል ቆጥረው ዳዊት ተማሩ ።

የቤተ ክህነት ትምህርታቸውን በጥልቀትና በስፋት ለማጠናቀቅ በ፲፱፻፲፪ ዓ/ም ወደ ጎንደር መጥተው በደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ ከታወቁት ዝነኛ መምህር ከመምህር መንክር የቅኔ ትምህርት ተማሩ ።

በዚያም ወደ ጋይንት አውራጃ ዙርአምባ አቡነ አረጋዊ በመሄድ በ፳ሺ ፲፱፻፲፬ ዓ/ም ከታላቁ ሊቅ ከመሪ ጌታ ታደገ ድጓ ከመሪጌታ መርዓዊ ዝማሬ መዋሥዕት ለአራት ዓመት ተምረው በሚገባ አውቀዋል።



ሊቀ መራህያን ይትባረክ እኚህ ነበሩ

ከዙራምባ ተመልሰው በወገራ አውራጃ ከመምህር ወልደ ዮሐንስ ጡዋ ጊዮርጊስ አቋቋም ተምረዋል ።

ከዚያም በተጠቀሰው አውራጃ ቧክስ ጊዮርጊስ ከተባለው ደብር ከመምህር ኅሐ ጽባህ ለሁለት ዓመት በተጨማሪ አቋቋም ተምረዋል ።

በ፲፱፻፳፩ ዓም ወደ ጎንደር ከተማ በመመለስ በደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ ከመምህር ፈለቀ ብሩ የአቋቋም ትምህርታቸውን ለአምስት ዓመታት አጠናቀው አውቀው በ፲፱፻፳፮ ዓ/ም በመምህራቸው ሙሉ ፈቃደኛነት ወንበር ተክለው ማስተማር ጀመሩ ።

ከዚያም በ፲፱፻፳፯ ዓ/ም የመሪ ጌትነት ማዕረግ በማግኘት ዕዋትወ ዜማና አቋቋም በደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ ማስተማራቸውን በሰፊው ቀጠሉ ።

በ፲፱፻፴፬ ዓ/ም ቀደም ሲል የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ወደሚባለው መሥሪያ ቤት ተዛውረው በጻድቁ ዮሐንስ ትምህርት ቤት የሃይማኖትና የቀለም ትምህርት ለሰባት ዓመታት በማስተማር ብዙ ሀገሪቱን የሚጠቅሙ ምሁራንን አፍርተዋል ።

በ፲፱፻፵፯ ዓ/ም በጊዜው በነበሩት በብፁዕ አቡነ ሚካኤል ትዕዛዝ ወደ ፈለገ ሕይወት መጻሕፍት ቤት በመዛወር አቋቋም እያስተማሩ ግምጃ ቤት ማርያም ከመምህር ክፍሌ ይመር በመማር አራቱን ወንጌል ትርጓሜ አጥንተዋል። ከዚያም ወደ ሌላ በመዛወር ከዶክተር አለቃ አየለ ዓለሙ በ፲፱፻፶፱ ዓ/ም የዳዊትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ተምረዋል ።

ሊቀ መራህያን ይትባረክ ገብረ ሚካኤል በጎንደር ከተማ ደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ በመሪጌትነት ለ፶፯ ዓመታት በቅንነትና በትጋት አገልግለዋል ።

### ከሠሯቸው ዓበይት ሥራዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

፩/ በአሥመራ ማኅበረ ሐዋርያት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ታቦት ሲገባ ቤተ ክህነትን ወክለው ከአቻ ጓደኞቻቸው ጋር በመገኘት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

፪/ በ፲፱፻፳፬ ዓ/ም አሥመራ ከተማ በተካሄደው ኤክስፖ



www.ethiopianorthodox.org

ተካፍለው ላበረከቱት ቁም ነገር የተሳትፎ ዲፕሎማ ተቀብለዋል ።

፫/ በብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ አመራር ጎጃም ክፍለ ሀገር ልዩ መጠሪያው ደብረ ገነት ኤልያስ ክብረ በዓል ተገኝተው የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል ።

፬ እንዲሁም በጣና ባህር የሚገኘው የእንጦራ ተክለ ሃይማኖት ታቦት ሲገባ ተገኝተው መንፈሳዊ ተግባርን ፈጽመዋል ።

ታላቁ ሊቅ ሊቀ መራህያን ይትባረክ ገ ሚካኤል የ፮ ወንዶችና የሦስት ሴቶች አባት ነበሩ ።

ታላቁ ሊቅ ሊቀ መራህያን ይትባረክ ገ ሚካኤል በሕይወት ዘመናቸው በነበራቸው ታላቅ ተሰጥዖ ብፁዓን ጳጳሳት ታላላቅ እንግዶች ወደ ጎንደር በመጡበት ወቅት ታሪክን ያገናዘበ ምሥጢር አዘል ግሥና ፡ ወረብ በመድረስ የሚቀበሉ ምሁር ነበሩ ።

እኒህ ታላቅ ሊቅ ሌት ከቀን በንቃት በማስተማር ብዙ ምሁራንን አፍርተው ለቤተ ክርስቲያናችን አበርክተው በተወለዱ ፹፱ ማስተማር በጀመሩ በ፶፮ ዓመታቸው ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። ሞት ለሁሉም በተራ የሚደርስ ነው ግን በሚሞተው ሥጋ የማይሞት መልካም ሥራ ሠርቶ ማለፍ እንደዚህ ያስመሰግናል ።

ስለዚህ እንደ ሊቀ መራህያን ይትባረክ ሁሉም ከአምላክ በታደለው ጸጋ መልካም ሥራ ሠርቶ ማለፍ ተተኪውን ትውልድ ደስ ያሰኛል ። ሊቀ መራህያን ይትባረክ በሥጋ ከቤተ ሰቦቻቸው ቢለዩም በመንፈስ ሕያው ስለሆኑ ቸሩ እግዚአብሔር ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን ለነፍሳቸው ዕረፍትን እንዲሰጥልን እንማፀናለን ።

### ለሟቹ የተደረሰ ቅኔ ስለ መሪጌታ ይትባረክ ገ ሚካኤል ዜና ዕረፍት ከቀኝ ጌታ አእምሮ ፈረደ የኃዘን መግለጫ ቅኔያት አዲስ አበባ

ጉባኤ ቃና ተላፀይ ቂርቆስ አምኀ
ዘንከ ዐጉረ ርእስከ ፍጡነ
ዕለተ ሞቱ ለሊቅ ፋሚካ እስመ
ጊዜ ብካይ ኮነ ።

(ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል)

# ጻድቃን ይወርስዋ ለምድር

ጻድቃን ተብለው የሚጠሩ እንዴት ያሉ ናቸው ? ጽድቅ ማለትስ ምን ማለት ነው ? የሚል ጥያቄ ቢኖር ፤ ጻድቃን ተብለው የሚጠሩ የኃጢአትን ተግባር ተጸይፈው በሃይማኖታቸው ጸንተው ክብርን ለመጐናጸፍ በፍና ጽድቅ የሚመላለሱ ናቸው ።

እነዚህ በዚህ መንገድ የሚመላለሱ ሁሉ ጻድቃን ተብለው ይጠራሉ ምድርንም ወርሰው ይኖራሉ።

ጽድቅ ማለትስ ምን ማለት ነው ለሚባለውም ፡ ጽድቅ ሁለት ትርጉም ወይም ሁለት ፍች አለው ፩ኛ ውሸት የሌለበትና ያልተቀላቀለበት እውነት አርግጠኛ ማለት ሲሆን ሁለተኛውም በሰማያዊ ክብር ከበረ (ተከበረ) ማለት ነው ፡ ጽድቅን ክብር ሲለው (እስመ ነአምር ከመ ኢይጸድቅ ስብእ በገቢረ ሕገ ኦሪት ዘእንበለ ዳዕሙ በአሚን በኢየሱስ ክርስቶስ) ትርጉሙ "በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው እንጂ ሰው ሁሉ ሕገ ኦሪትን በመፈጸም እንዳይከበር እናውቃለንና ይላል ገላ ፪ ፡ ፲፮ ።

ጽድቅን እውነት ሲለው ደግሞ (ባህለ ኢሳይያስ ጸድቀ) በዕብ ሕዝብ የኢሳይያስ አባባል የኢሳይያስ አነጋገር በሕዝቡ ዘንድ ጸደቀ እውነት ሆነ ተረጋገጠ ማለት ነው።

ከዚህም ላይ ልንጽፍበት የምንፈልገው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ሁሉ በእምነት እንጂ ሕግን በመፈጸም የማይከብር መሆኑን በጻፈው መሠረት ነው ።

ጻድቃን የሁለቱ ዓለማት ወራሾች ናቸው ለማለት እንችላለን ምድርን ወርሰዋት ይኖራሉ መንግሥተ ሰማያትም ገንዘባቸው ናት የተዘጋጀችው ለእነሱ ናትና ።

ጻድቃን ምድርን ሊወርስዋት የሚችሉት በሥጋዊ ኃይል ጦር በመወርወር ሥጋዊ መሳሪያን በመያዝ ወይም እነዚህ በመሳሰሉት ነገሮች ሳይሆን በእውነተኛነታቸው በመልካም አርአያነታቸው በአካሄዳቸውና በሰላማዊ አቀዋማቸው ነው ።

ከዚህ የተነሣ የሄዱበትና እግራቸው የረገጡት ሁሉ ሀገራቸው ቦታቸውና ርስታቸው ነው ።

ጻድቃን በቀለም እኛን አትመስሉም በቋንቋም ከእኛ ጋር አትግባቡም ብሎ የሚቃወማቸው ሰው አይኖርም ይኸውም በፊታቸው ያገኙት ሰው ሁሉ ወንድማቸው ሲሆን የተረገጡትም ምድር ሀገራቸው ስለሚሆን ነው ።

ጻድቃን ከበቁና ከነጽሮተ ሥሉሥ ቅዱስ ሲደርሱ ሰማያዊ ኃይልና ሰማያዊ ጸጋ ስለሚሰጣቸው አውሮፓውያንም ቢሆኑ አፍሪካውያን በመካከላቸው የዘር ልዩነት ሊፈጠር አይችልም ኤውሮፓዊ ወደ አፍሪካ ቢሄድ ወይም አፍሪካዊ ወደ ኤውሮፓ ቢሄድ ከሀገራችን ልቀቅ የሚለው ሰው የለም ። ምንም እንኳን በተፈጥሮአችን ከአንድ አባት ከአዳም ከአንዲት እናት ከሔዋን በመወለድ ወንድማማቾች ብንሆንና በአንድ በክርስቶስ በማመንም የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባሎች ብንሆንም እያንዳንዳችን የተለያየ ሀገር እንዳለን በመልክም የተለያየ ቀለም መኖራችን የታወቀ ነው ።

በዚህ መሠረት ከሀገራችን ወጥተው በባዕድ (በውጭ) ሀገር ከሚኖሩ ጻድቃን አንዳንድ ብንጠቅስ መልካም ይመስለናል ። ፩ኛ አፍሪካዊውና ኢትዮጵያዊው አቡነ ኤዎስ ጣቴዎስ ከኢትዮጵያ ወደ አርማንያ ሄደው አርማንያንን በማስተማርና ሕዝቡን በመምከር ከፍተኛ የማስተማር መስዋዕትነት በመክፈል ከአርማንያ ሕዝብ አንዱ እንደ ነበሩና በዚያው በአርማንያ አርፈው ቤተ ክርስቲያን ታንፃላቸው ጽላት ተቀርጾላቸው አርማንያን ወርሰው መኖራቸውን ሁሉ ያውቃል ።

በዚህ አንጻር ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢትዮጵያውያንን በማስተማር የኢትዮጵያን ምድር ወርሰው ስማቸውን አስጠርተው በስማቸው አብያተ ክርስቲያናት ታንጸውላቸው የሚኖሩም እንዳሉና በእነዚህም መካከል አቡነ አረጋዊንና ቅዱስ ገብረ ክርስቶስን እንጠቅሳለን ። እነዚህ ቅዱሳንም ምንም እንኳን የትውልድ ሀገራቸው ኤውሮፓ ቢሆንም በተለይ አቡነ አረጋዊ ከኤውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በማስተማራቸው ከኢትዮጵያውያን እንደ አንዱ ተቆጥረው በኢትዮጵያ በ፲፬ አህጉረ ስብከቶች በመንፈሳዊ ስም የሚጠሩበት ቤተ ክርስቲያን ታንጾላቸው ጽላት ተቀርጾላቸው ምድርን ወርሰው እንዳለ የምናይበት ዓይናችን መስክራችን ነው ።

ጻድቁ አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ስማቸው በከፍተኛ አጠራር ሊጠራ የቻለውና ምድርንም ሊወርሱ የቻሉት ከሥጋዊና ከደማዊ አርበኛ ተዋግተው ሳይሆን በአራት መዓዘን ካሉና ዓለመ ጽልመት ከሚገዙ ከአጋንንት ጋር በመዋጋት ነው ጻድቁ አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ሁለቱም የታላላቅ ሰዎች ልጆች እንደነበሩ እያንዳንዳቸው ገድል ይናገራል ነገር ግን እነዚህ ጻድቃን የዓለምን ኀልፈት በመገንዘብ ሰው በዚህ ዓለም እየበላ እየጠጣ እየለበሰና እያጌጠ ቢኖር በፍጻሜ ዘመኑ ግን በነፍሱ ከተጐዳ ጥቅሙ ምንድን ነው ? በሚል መንፈሳዊ ሐሳብ ተነሣሥተው ዓለሙን ንቀውና አቃልለው ቤት ንብረታቸውን ትተው መሄዳቸውን የሕይወታቸውን ታሪክ የሚናገረው ይገልጽልናል ።

ጻድቁ አቡነ አረጋዊ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ፱ ራሳቸው ነው እንጂ ብቻቸውን አልነበሩም የገቡበትም ዘመን በስድስተኛው ምእት ዓመት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ነው እንዲያውም አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሰዓታት በተባለው ድርሰታቸው ፱ ቅዱሳን ሮማውያን ሲሉ አስታውሷቸው ይገኛሉ ።

እነዚህ ቅዱሳን አቡነ አረጋዊን መሪ በማድረግ በኢትዮጵያ የወንጌልን ብርሃን አብርተው አርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ሃይማኖትንም ሊያስፋፉ ችለዋል ከዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ ምእመናን ትምህርተ ወንጌል ስለ ተሰበከላቸውና በእነ አቡነ አረጋዊም የእግዚአብሔርን ቃል ተመግበው ከዶብስተ ኃጢአት ወደ ልምላሜ ንሥሐ ከልምላሜ ንሥሐ ወደ ጽጌ ትሩፋት ከጽጌ ትሩፋትም ወደ ፍሬ ክብር ለመድረስ ችለዋል ።

እነ አቡነ አረጋዊ ምንም እንኳን የውጭ ሀገር ተወላጆች ቢሆኑም ቀና ብሎ በጥላቻ መንፈስ የሚመለከታቸው አልነበረም ጻድቃን ምድርን ይወርስዋታል ተብሎ የሚነገርላቸውም ስለዚህ ነው ።

በዚህ መልክ ከኖሩ በኋላ ጻድቁ አቡነ አረጋዊ በትግራይ ክፍለ ሀገር በአድዋ አውራጃ ደብረ ዳሞ የተባለውን ገዳም መሥርተውና የአንድነትን ገዳም አቋቁመው ከፈጣሪያቸው ስማቸውን የጠራ ሁሉ እሳቸው ከገቡበት ውሳጤ መንጦላዕት እንዲገባ ቃል ኪዳን ተቀብለው ጥቅምት ፲፬ ቀን መሠወራቸው ይነገራል ።

ይህ ብቻ አይደለም ጻድቃን ይወርስዋ ለምድር በተባለው መሠረት የጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በኢትዮጵያ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ እየተዘዋወሩ ወንጌልን በማስተማራቸው እነሆ በመላ ኢትዮጵያ በስማቸው አብያተ ክርስቲያናት ታንጸውላቸው የኢትዮጵያን ምድር ወርሰው ይገኛሉ ።

ጻድቃን ይወርስዋ ለምድር ቢባልም ጻድቃን ምድርን ብቻ ወርሰው የሚቀሩ አይደሉም ። በሠሩበትና የማስተማርን መሥዋዕትነት የከፈሉበትን በማስታወስ እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መን





www.ethiopianorthodox.org

ግሥት ውረሱ ተብሎ የተነገረላቸ ውንም መንግሥተ ሰማያትን ጭምር ይወርሳሉ እንጂ በዚህ አማካይነት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በኢትዮጵያ ዞረው ወን ጌልን ሲያስተምሩ በአንዳንድ ቦታም በጾምና በጸሎት ተወስነው ሱባዔ ሲያደርጉና ስለ ኢትዮጵያ ሆነ ስለ መላው ዓለምም ስለ ሰላም ሲጸልዩ ፳፻ ዘመን ከቆዩ በኋላ መጋቢት ፳ ቀን ከድካም ወደ ዕረፍት ተሸጋግሯል ።

እንግዲህ ጻድቃን ምድርን ይወ ርስዎታል በሚል ርእስ አቡነ አረ ጋዊ ቅዱስ ገብረ ክርስቶስንና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አነ ሣን እንጂ ጻድቃን ምድርን ይወር ስዋታል የተባሉት ጻድቃን ሁሉ በምድር ላይ በሠሩት መንፈሳዊ ሥራ መንግሥተ ሰማያትን ይወር ሳሉ ማለታችን ነው ።

ጻድቃን ሕይወታቸውን ለእግ ዚአብሔር ሰጥተው ሃይማኖታቸ ውን ጠብቀው ስለሚኖሩና እግዚ አብሔርም የለመኑትን ሁሉ እን ዲፈጽምላቸው ሲያረጋግጥ እው ነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን ሁሉ እኔ የምሠራውን ሥራ ሊሠራ ይችላል ሲል በሰ ጠው አምላካዊ ቃል መሠረት ስለ አምላክ አረጋዊ ስለ አምላክ ገብረ ክርስቶስ ስለ አምላክ ገብረ መን ፈስ ቅዱስ ብሎ እምነቱን በእግዚ አብሔር አድርጎ በእነዚህ ጻድ ቃን ስም የሚማፀን ዋጋው እንደ ማይጐድልበትና እንደማይቀር በት በማቴ· ፲ ፡ ፵፩ — ፵፪ ተጽፎ ይገኛል ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ ።

# ዜና ሊቃውንት

(ከገጽ ፲፩ የዞረ)

ትርጉም፡ ቂርቆስ ከ፡ንዘንህ የተነግ በፍጥነት ጠጉርህን ተላጭ ይትባረክ የሞቱ ቀን ፋሚካ የልቅሶ ጊዜን ሆኖአልና ።

ሥላሴ፡ መዋሥዕት ወዝማሬ

ለይትባረክ ያሬድ አርድእተ ሕጉ ፡
እምደብረ መንክራት ተሰዱ ይእዜ በኀዘን አንብዕ ዘሎሙ
ኢይንበሩ አምጣነ ተነሥተ ይትባረክ ቤቶሙ
ህየንተ ፍሥሐ ኀዘነ በዓሉ ዕለተ ፋሚካ ኮኖሙ
ወሥጋ ይብልዑ ኢተክህሎሙ
መንገለ ዙር አንባ ይሑሩ በዘይጸውሙ
እስመ ዛቲ ቀዳሚት እሞሙ ።

ትርጉም፡ ዝማሬና መሥዋዕት
ለያሬድ ይትባረክ የሕጉ ተማሪዎች የሆኑ
ዛሬ ከደብረ መንክራት ሁላቸው በዕንባ ኀዘን ተሰደዱ
እንዳይቀመጡ ቤታቸው ይትባረክ ፈርሶአልና
የፋሚካ በዓል ቀን በደሥታ ፈንታ ኀዘን ሆናቸው
ሥጋም ይበሉ ዘንድ አልተቻላቸውም
ስለ ጾሙ ወደ ዙር አንባ ይሒዱ
የመጀመሪያይቱ እናታቸው ያች ናትና ።

መወድስ፡ ማዕበለ ዝናም ሞት በጊዜ ወረደ
ትዕይንተ ጐንደር መልዑ በማየ ኀዘን አፍላጊሃ ።
ሰርወ ሊቃውንት አዕዋም እስመ አምአድባራት ተመ ልሃ
ወእንዘ ይጸውሩ የሐውሩ ፡
በምሥራቅ ፈለገ አንገረብ ወምዕራብ ቀሃ
ወእንበለ አዐድ ሊቃውንት ፡
አምጣነ አልቦሙ ክብር ትዕይንተ ጐንደር አድባራቲሃ
ጐንደርሂ ኀዘነ ልባ እንተ ፈድፋደ ወበዝኃ
እስመ እንዘ የሐልቅ ኢይሜኒ ኮነ ፍጻሜሃ (ኩለንታሃ)
ወምስለ ዝኒ ነገር ከመ ተነግረ ላዕሌሃ
እስመ ጠፍአ እምአብርሆ ሊቃውንት ብርሃናቲሃ

ትርጉም፡ የሞት ዝናም ማዕበል በወረደ ጊዜ
የጎንደር ከተማ ወንዞች በኀዘን ውሃ ሞሉ
የሊቃውንት ዛፎች ስር ከአድባራት ተነቅሏልና
እየተሸከሙም ይሔዳሉ ።
በምሥራቅ አንገረብ በምዕራብም ቀሃ (የተባሉ ወን ዞች)
ያሉ ሊቃውንት አዐድም
የጎንደር ከተማ አድባራቶቿ ክብር የላቸውምና
ጐንደርም የልቧ ኀዘን የበረከተና የበዛ ነው



www.ethiopianorthodox.org

መጨረሻዋ (ሁለመናዋ) ሲያልቅ አያምርምና
የዚህንም ነገር ምሳሌ በላይዋ እንደ ተነገረ
ብርሃኖቿ ሊቃውንት ከማብራት ጠፍተዋልና
የማኅሌት መብራቷ ብርሃን ይትባረክም ጨልሟል
ብርሃኖቿ ሊቃውንት ከማብራት ጨልመዋልና።

ከመምህር ሄኖክ ወልደ ሚካኤል
ጎንደር በዓታ የአቋቋም ምስክር
መምህር

ዘአምላኪየ፡ ሀብተ ሥላሴ ኪሩቤል ኀዋሳቲክ ኀበረ
የሐውሩ ኀበ ቀዳማዊ ማስያስ ዘሖረ
እስመ ለሊሁ አዘዘ እሎንተ ከመይጹሩ መንበረ ።

ትርጉም፡ ኪሩቤል ሀብተ ሥላሴ ስውነቶችህ በአንድነት
የመጀመሪያው ማስያስ ወደ ሔደው ይሔዳሉ
መንበርን ይሸከሙ ዘንድ እነሱን እሱ አዟልና ።

ዘአምላኪየ፡ ፪. የመሪጌታ አዳሙ አደባባይ ኢየሱስ ።
ፍሬ ሃይማኖት ምድረ ሀብተ ሥላሴ ነገሬ ።
ሞት ዕኀለ መዋቲ ያነሥእ ዘተርፈ
እስመ ለዘሬእ ሕማም ነሚእ ለዘዚአሁ ሐለፈ ።

ትርጉም፡ በምድር የረገፈ የሃይማኖት ፍሬ ሀብተ ሥላሴ
የቀረን የሚች ልጅ ሞት ያነሣል
ለዘሬ ሕማም ይዞ ለርሱ አልፏልና ።

ዘአምላኪየ፡ ፫. ዘመምህር ወልደ ሰንበት ግምጃ ቤት ማርያም የሐዲስ
መምህር
ሀብተ ሥላሴ ዘኮነ ሐዋጼ ሕንፃ ደብር ልዑል
ለሞት ሕንፃ አበዊነ ርኢክዎ ይብል
ባህቱ ድኅረተ ብከየ ወሊድ ባህል

ትርጉም፡ ከፍ ያለ የደብር ሕንፃ ጉብኚ የሆነ ሀብተ ሥላሴ
የአባቶቻችን ሕንፃ ሞትን አየሁት ይላል ።
ነገር ግን የልጆች ባህል ለቅሶ ወደኋላ ታየው ።

ዘአምላኪየ፡ ፬ ዘአለቃ ላዕከ ማርያም የፊት አቦ አለቃ የነበሩ
እምድኅረ ልደቱ ክብርት ዘደብረ መንክራት ተግህዶ
ዘዮም ወልደ ኢየሉጣ መጠወ ክሳዶ
እስመ አዘዞ መቅደመ ፈጣሪ አሜን ትንግኤ ተዘምዶ ።

ትርጉም፡ ከክብርት ልደቱ በኋላ የደብረ መንክራት መገለጥ
የዛሬው የኢየሉጣ ልጅ አንገቱን ሰጠ
የትንግኤ ተዘምዶ እምነትን በመጀመሪያ ፈጣሬ አዞታልና ።

ዘይእዜ፡ ፭. የመምህር ሄኖክ ወልደ ሚካኤል
ይመና መቅበርተ እንዘ ይሬሲ
ወበብርሃኑ ለነግድ እንዘ ያበርህ ሌሊተ ፡
ለሕዋሳተ ሊቀ ሕዝበ ሙሴ ፡ መልአከ ዕለተ ትንግኤ
መርሆሙ መዓልተ ። ወገባሬ በዓል ዓቢይ ገቢረ

# እናስተዋውቃችሁ

በዛሬው እናስተዋውቃችሁ ጽሑፋችን ከባለታሪኩ ደብር ከሸ ው፡ን ቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ይሆናል የሸውን ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክር ስቲያን የሚገኘው በደቡብ ጎን ደር አውራጃ ውስጥ ዝርጋ ይባ ላል። ይህ ደብር የተተከለው በ፩ሺ፱፻፸፯ ዓ·ም ነው ከተተከለ ፰፻፹፯ ዕድሜ ያለው ባለታሪክ የሆነ ቤተ ክርስቲያን ነው ማስረ ጃውም ታሪክ መዝገብ ከአብያተ ክርስቲያናት ተራ ቁጥር ፪ሺ፱፻፶፩ ተመዝግቦ ይገኛል ይህንንም በቤተ ክህነት መዝገብ ተመልክቶ ለመረዳት ይቻላል የሸ ው፡ን ቅዱስ ጊዮርጊስ አቀማመጡ ከመልካም ቦታ ይሁን እንጂ በማ ንኛውም ቦታ ላይ ሆኖ የሚታይ አይደለም ቢታይም ለየኳስ አቦ እና ለጀንባ ተክለ ሃይማኖት ሲሆን ዙሪያው በበረሐ ዛፎች የተከበበ በመሆኑ በአካባቢው ያሉት ዛፎች ምንጊዜም ከረም ትና በጋ የለመለሙና ከለምለም ቅጠሎቻቸው ላይ ንቦች መልካም ድምፃቸውን ሲያሰሙና እንደስኔ ደመና ሲያንዣብቡ ያለማቋረጥ ይታያሉ በቤተ ክርስቲያኑም ንብ በብዛት ይኖራል በተለይም ቤተ መቅደሱ የንብ መኖሪያ ነው የሚ ከበረውም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚያዝያ ቅ/ጊዮርጊስ ሲሆን በዚህም ጊዜ በእስቴ ፡ በፋርጣ ፡ በምክሬ በአንዳቤት ፡ በላይ ጋይ ንት በስማዳ በአማሐራ ሳይ ንት በኮሬብ በሙጃ ያሉት ያሉት መምህራንና ሊቃውንት ተሰብስበው ንቦቹ በአንድ ጐን በመልካም ድምፃቸው ታቦቱን እየዞሩ ሲያወዱት ሊቃውንቱ



www.ethiopianorthodox.org

ደግሞ ስብሐተ ማኅሌቱን ሲያሳ ምሩት አድረው ይውላሉ ታቦ ቱም በሚዞርበት ጊዜ ንቡ አብሮ ይዞራል ።

## ትዝታውና አስደናቂ ታሪኩ ፡

ትዝታው የቅንጭቡ ፡ የአንቀ ባው ፡ የግራሩ ፡ የወይራው ፡ የቸፈራው የቁልቋሉ ፡ የደረው የነዚህ ዛፎች አቀማመጣቸው የማይረሳ ትዝታ አለው ከነዚህም ላይ የሚያንዣብበውና ድምፁን ከፍ አድርጐ የሚያሰማው የንብ ብዛት የአካባቢውም ምእመናንና የዕንግዳ ተቀባይነታቸው ከፍተኛ ትዝታ ነው ።

የቆየ ታሪኩ ደግሞ ሕዝቡ ሲለ ምነው ግንድ አንሴ ፡ አሞራ ቀልቤ ፡ ብር በንቅቡ ንብ በዱሩ በረኸኛው እያለ ሲለምኑት ፈጥኖ ይደርስላቸዋል ። የዚህም የአለማመን ታሪኩ ግንድ አንሴ የተባለበት ምክንያት እንዲት ሴት አንድ ግፈኛና ቀማኛ ባለሥ ልጣን እርስቷን ቀምቷት ያለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ረድኤና ዳኛ የሌ ላት በቀጥታ እያለቀሰች ኼዳ ብቻ ዋን ወደ ቤተ መቅደሱ በር ገብታ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንኳንስ ርስቴን በግፍ የወሰደብኝን ሰው ለማስመ ለስ እዚህ ተቆርጠው የወደቁትን እንጨቶች ሳይቀር ታለመልማቸ ዋለህ ብዬ ነው የማምነው ዛሬ ግን ተበደልኩ ተቀማሁ ርስቴ ሲወሰ ድብኝ እንዴት ዝም ትላለህ ብላ ስታለቅስ የቅዱሰ ጊዮርጊስ ሥዕል ዕፉ አውጥቶ አንቺ ሴት አታልቅሽ [illegible] [illegible] ልቅሶሽ ወደቤትሽ ሲል ቅዱስ ጊ ዮርጊስ ተናግሮ አጠገቡ ለሦስት ማቶ ዘመን ወድቆ የኖረውን ግንድ አለምልሞ አሳይቶአታል ። በዚህ ግንድ አንሴ ተብሎአል እር ሷም ወደ ቤቷ ስትኼድ ባለፀጋው ንና ዳኛውን እርስቷን የወሰደባ ትን ሰው ሞቶ ዘመዶቹ ሲላቀሱ ደርሳለች መሬቷንም አግኝታለች ዕንባ ታላቅ የጦር መሳሪያ ነው

በዓል ኢያስተተ ፡ በዘኢተክሥተ ጽርሀ ወበ ዘተከ ሥተ፡
አምጣነ ጸውዓ ቴርቶስ ለምስሐ በዓል ዓበይተ ።

ትርጉም፡ መታብሩን ደመና ሲያደርግ
በብርሃኑም ለእንግዳ በሌሊት ሲያበራ
ለሰውነቶች አለቃ ሙሴ ወገኖች
የትንግሌ ዕለት መልአክ በቀን መሪቸው
ታላቅ በዓል ሥሪም በዓል ማድረግን ላስታጉለም
በተገለጠው አዳራሽና በአልተገለጠው (አዳራሽ)

ለምሳ በዓል ቴርቶስ ታላላቆችን ጠርቷልና ።

እንዚህን ቅኔዎች የግዕዝ ቋንቋቸውን ወደ አማርኛ ለመተር ጐም የፈለግሁት አንባቢው የሥነ ድርሰቱን ምሥጢር በሚያው ቀው የአማርኛ ቋንቋ እንዲረዳው በማለት ስለሆነ ምናልባት የአተረጓጐሙ መንፈስ ከቅኔው ደራሲ መንፈስ ውጭ መስሎ ቢታይ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። በዚህ አጋጣሚም ባለቅኔዎችን መምህራን ሊቃውንት አመሰግናለሁ ።

ቀ.ጌ. አዕምሮ ፈረደ አ.አ

ይሉሀል ይህ ነው አሞራ ቀልቤ የተባለበትም ምክንያት አሞሮቹ የትም የትም በረው ሲኼዱ አንድ አሞራ ዓይኑ ጠፍቶ ከግቢው ዛፍ ላይ በማረፍ ምግቡን ቅዱስ ጊዮር ጊስ እያመጣለት ሲመገብ ከአንድ ዛፍ ስር ሳይንቀሳቀስ ፪ ዓመት ተቀምጦአል የእግዚአብሔር ታላቅ ድንቅ ሥራ ይሉሐል ይህ ነው ።

ብር በንቅቡ ማለት ሚያዝያ ፳፫ ቀን በየዓመቱ የቅዱስ ጊዮር ጊስ ዐረፍቱ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ያስዕለት ዕቃዎች ሲገቡ ለዕ ጣኑ መሰብሰቢያ በባለ ሙያዎች የተሰፋ ትልቅ ድርብ ይቀመጣል በዚያ ላይ ዕጣኑ ይደረጋል ። [illegible]ልዘቢቡ ደግሞ (ቆለምቻሽ ባለ ግራም የስፌት ጠረጴዛ ሞሰብ ሚሰል) ይደረግና በዚያ ዘቢቡ ይሰበሰባል ብሩ ደግሞ በጣም ትልቅ እንቅብ (50 ኪሎ እህል የሚይዝ) ስፌት ይቀመጣል ብሩ የማርትሬዛው ነጭ ሽልንግ በየዓ ይነቱ በዚያ ላይ ይደረጋል ይሞ ላል ደግመው ሌላ ያደርጋሉ ለዚህ ነው ብር በዕንቅቡ የተባለበት ምክንያት እንደዚህ ዓይነት የስእ ለት ተቀባይነት በየትም የለም እንደአጋጣሚ ስእለቱን ካነገን ዘንድ ስለአቀማመጡም እንጠቅሳ ለን ይህ ገንዘብ በጭቃ ሹሙ በገበዙ በመሪጌታው ተቆጥሮ እዚ ያው ከቤተ መቅደሱ ይቀመጣል የሚነካውም የለም እንኳንስ ገንዘ ቡን የወሰደውን ይቅርና በቤተ መቅደሱ ውስጥ ጢፍ ተንዷል ሳያጠፋ የኼደውን ዲያቆን ወይም ቄስ አያስኬደውም በፊቱ ይከበ ዋል ። እንቢ ብሎ ቢኼድ ፊቱን ይበላዋል ይህ እስከዛሬ ድረስ ያለ ታሪክ የሚታይ ሲሆን ገንዘቡ ደግሞ በሙሐሩ ላይ ይቀመጣል



የሚነካውም የለም ንቡ በዱሩ የተባለውም ከመቅደሱ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ በአሉት ዛፎች ላይ በሙሉ ንብ ብቻ ስለሚ ታይ ነው የሰው ሀብት ያልቀማ በሐሰት ያልማለ ነፍስ ያልገደለ ያልሰረቀ ንጹህ ሰው ከዕድሞው ውጭ ዙሪያ ካለው ንብ ማር መቁ ረጥ ይችላል ግን አይሸጥም አይለ ወጥም ለምግብ ብቻ ይጠቀሙበ ታል አንድ ቀን አንድ ሰው የሸ ውኃ ጊዮርጊስ ስእለት ይሰማል መባሉን ስለሰማ በዘመኑ በጣም እህል በብዛት ሃገሩ ይዞ ስለነበር እንበጣ መጣ በዚህ ጊዜ በልመና በሬ አርሶ የዘራውን እህል የአንበ ጣው መንጋ እንዳይበላበት በቅን ልቡና በትሑት ሰብእና ለሸውኃ ጊዮርጊስ ይህንን አንበጣ እህሌን እንዳይበላብኝ የተከላከልክልኝ እንደሆነ አንድ ብር ቋጥሬ በእግሬ ተጉዠ ለሚያዝያ ጊዮርጊስ ይገ ልህ እመጣለሁ ብሎ ተሳለ ታላቁ ሰማዕት ቅዱስ ጊዮርጊስም የድሐ ውን ልመና ተቀብሎ የመጣው አንበጣ እህሉን በሙሉ በልቶ ሲሄድ የርሱን ብቻ ሳይበላበት ቀረ በዚህም ምክንያት የተሳለ ውን ብር ቋጥሮ ጉዞውን ከአንድ መንገደኛ ጋር ወደ ሸውኃ ጊዮር ጊስ ሲቀጥል ጓደኛው ስለደከ መው በረሐውን እንዳይሄድ አስቦ ስማዳ አንፋርጌ ጊዮርጊስ ነው አንድ ነው ለዚሁ ስጥተን እንመ ለስ አለው ያ የተሳለው ሰውዬ በንግግሩ ተስማምቶ በነጭ መሐ ረም የተቋጠረውን የማርትሬዛ ብሩን ከኪሱ አውጥቶ ላልተሳለ በት ለአንፋርጌ ጊዮርጊስ ሊሰጥ ሲል ነጭ አሞራ መጥቶ ከእጁ ላይ ነጥቆ ወስዶ ሸውኃ ጊዮርጊስ ከእ ንቅቡ ላይ ጣለው ሰውየውም ስእ ለት የተሳለው በነገሩ ተደናግጦ ጉዞውን ወደሸውኃ ጊዮርጊስ ቀጠለ ከቤተክርስቲያኑም ሲደ ርሱ ከስእለት መቀበያ ሲያይ ስሙ የተጻፈባትን ያችን ነጭ ጨርቅ ተመልክቶ የእርሱ ብር እንደተቋጠረ ተቀምጦ አገኘ ሕዝ ቡም አሞራው አምጥቶ ሲያስቀ ምጥ ይመለከቱ ስለነበረ ነገሩ የገ ቢረ ተአምር መሆኑን ተረዱ ይህም ታሪክ የተፈጸመው በ፲፱፻፳፬ ሚያ ዝያ ፳፫ ቀን ነው ያም እዚህ እንስጥ ያለም ሰው ወዲያውኑ እንዳይናገር እንደበቱ ተዘጋ ኼዶ ሲሳልም አፉ ተከፈተለት ይላል ስእለት ሲሳሉ የአንዱን ከአንዱ መደባለት አይገባም እስቲ ስለ ስእለት መሳል ቅዱሳት መጻሕፍ ትን እንመርምርና እንረዳ።

የሸውኃ ቅዱስ ጊዮርጊስን የቅ ርብ ጊዜ አስደናቂ ታሪክ እንመል ከት በሀገራችን ሰርግ ሰው ሲያደ ርግ የሙሽራው ሚዜዎች በበነ ጋው እየዞሩ በየመንደሩ ጨዋታ ይጫወታሉ ይዘፍናሉ ? በዚህ ጊዜ ቅቤ ያለው ቅቤ ዶሮ ያለው ዶሮ ፍየል ያለው ፍየል የቻለ በሚዜዎች ቁጥር ያልቻለ እንደአ ቅሙ ይሰጣቸዋል ይህ የሃገር ባህል ስለሆነ ነውርነትም ነቀፈ ታም የለበትም ስለዚህም በ፲፱፻፶፭ ዓ.ም በአካባቢው የድርቅ ዘመን ስለሆነ የሚታለብም ላም የረባም ዶሮ ጠፋ በዘመኑም አንድ ባለፀጋ ልጁን ይድር ስለነበረ ሀብታም በመሆኑ ልጁ ፳፬ ሚዜዎች አሉት እርሱ በሃገሩ ደንብ መሠረት ፫ቱ ጫጉላውን ሲጠብቁ ፳ው እየዞሩ ሲጫወቱና ሲዘፍኑ ድርቅ በመ ሆኑ ዶሮም ቅቤም የሚሰጥ እንብ ዛም አልተገኘም በዚህም ምክን ያት ሚዜዎቹ በጣም አዘኑ ሚዜው ዲያቆን ስለነበረ ወንድ ሞቹ ለሸውኃ ጊዮርጊስ እንዝፈን ለት እርሱንም አምላኩንም እናመ ስግነው የሚል ሃሳብ አቀረበ በአ ሳቡ ተስማምተው ኼደው ከቤተ ክርስቲያኑ በር ለይ ሆነው ቢዘፍ ኑና ቢጫወቱ ለሙሽራይቱና ለሙሽራው ለቁነትም ሚዜዎች ጭምር ለእያንዳንዳቸው አንድ ጊዜ አብርሮ ይዞ አምጥቶ በድምሩ ፳፬ ቆቅ ሰጥቶአቸዋል ። ከዚያም በፊት ድርቅ ሲሆን ለረሐብተ ኞች ባሕታውያንና መምህራን ጅግራ ቆቅ እያስገረና እየያዘ እያ መጣ ይሰጣቸው እንደነበረ ይነገ ራል በበረሀ ላይ ተቀምጦ የሰውን ልጅ መመገብ በጣም ዕፁብ አስደ ናቂ ታሪክ ነው እስቲ ሸውኃን የምታውቁ ያያችሁትንና የሰማች ሁትን መስክሩ አስታውሱት ጕጃ ምና ጕንደር ወሎን ዋድላና ደላን ታን ያየና የዞረ ተማሪ የሸውኃ ቅዱስ ጊዮርጊስን ሳይጎበኝና ሳያይ አይመጣም መቼም ሃገራ ችን በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢ ነት የተባረከች የታደለች ሃገር መሆኗ እሙን ነው የሸውኃ ጊዮር ጊስ የተባለበት ምክንያት እንዳ ንድ ባለታሪኮች እንደሚተርቱት አሸናሽተና የሚባሉ ዛፎች የአሉ በት ስለሆነ በነዚህ ዛፎች ምክን ያት ሸውኃ ተባለ ይላሉ ዙሪያ ውም ውኃ ብቻ ነው አንዳንድ ጸሐፊዎች ደግሞ ከቤተ ክርስቲ ያኑ አጠገብ ምንጭ ውኃ ስለአለ ግራኝን የሸሹ ኢትዮጵያውያን በሸውኃ ጊዮርጊስ ተቀምጠው ስለነበረ ሰዎቹ ሲሆኑ ሺህ በቅሎ ፡ ሺህ ግመል ፡ ሺህ አህያ ጭነው ስለነበረ እነዚህ እንስሳት በሙሉ በየተራ ሲጠጡ ውኃው ምንጩ የሚፈልቀው እየበዛ ይሄዳል እንጂ የማያልቅ ሆኖ ስለተገኘ ሺህ ቀላቢ ሺ ጉድጓድ ውሃ ተባለ በዚህም ምክንያት ሸ ውኃ ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ጊዮርጊስ ተብሎ ተጠራ ለዚህ ነው በርእሱ እናስተዋውቃችሁ ያለንበት ምክንያት በ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. በሚያዝያ ፳፫ ቀን የተደረገው ተአምር የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ ወ/ሮ ንግሥት ብርሃን የተባሉት እናት ለቅዱስ ጊዮርጊስ ተስለው ከደጃቸው ላይ አንድ ቀፎ ያኖራሉ በዚህም ጊዜ ንቡ ግር ብሎ ከቀፎው ውስጥ ይገባል ርሳቸውም ማርማሩን እየቆረጡ ሲሸጡ ሰም ሰሙን ደግሞ ሳይሸጡ በተባሉት መሠረት ሲሰጡ ቀፎውም ከአንድ ወደ አርባ ቀፎ ደረሰ በዚህም ጊዜ አንድ ጐረቤታቸው የሆኑ ተስፋ ለማኅበሬ የማበራው ሰም ስለአጣሁ እባክሽን ስጭኝ ብለው ሲለምኑአቸው ረስተው ለጊዮርጊስ የሚሰጡትን ሰም ተሳስተው በሙሉ ለሰውየው ሰጡት ለጊዮርጊስ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ዋዜማ የሚልኩት ሰም ስለቀረበት አርባውም ቀፎ ንብ ወጥቶ ኼደ ቀፎው ብቻውን ቀረ ርሳቸውም ጢት ታቦቱ ሲወጣ ኼደው እያለቀሱ የሰጠኸኝን አትንሳኝ ንቡን መልስልኝ በየዓመቱም የምሰጠውን ስእለቱን እንደልማዴ አመጣለሁ ብለው ከታቦቱ ስር ተደፍተው አልቅሰው እቤታቸው ቢኼዱ የሀርባው ቀፎ ንብ መጥቶ ገብቶ አገኙት አሁንም በሕይወት አሉ ንቡም አለ ተደስተው ይኖራሉ እምነት ይህንን ያደርጋል የበለጠም ያደርጋል እምነት ከፍተኛ መሳሪያ ነው ፪ኛ በሰማዳ ወረዳ በላይ ሙጃ ወስጥ የሚኖሩ አርሶ አደር ገበሬ የሆኑ አቶ ሞገስ መብራቴ የተባሉት ለንግድ ወደ ነፋስ መውጫ ጨጨሆ ሄደው ሳሉ ሦስት ሽፍቶች ንብረታቸውን ሲዘርፉአቸው በጣም በመጨነቅ የሸውጋ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከነዚህ አድነኝ ድረስልኝ ካዳንከኝም ለሚያዝያ ፳፫ ቀን ለዋዜማህ በሬ አርድልሀለሁ ብሎ ተሳለ እንደተሳለም ወዲያውኑ ለአንደኛው ሽፍታ ቅዱስ ጊዮርጊስ በራዕይ ይገለፅና የዚህን ሰው ንጹሕ ገንዘብ መልሱ ይላቸዋል እርሱም የታየውን ራዕይ ለጓደኞቹ ነገራቸው እርሱም ጓደኛቸው ሲነግራቸው ሁሉም ተደናግጠው ገንዘቡን ይመልሳሉ ይህ የተደረገው መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ነበር ከዚያም በኋላ ስእለቱን የተሳሉት አቶ ሞገስ መብራቴ የተባሉት ግለሰብ ስእለታቸው ስለደረሰ የእርሻ በሬአቸውን ወዲያውኑ ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ነድተው ወስደው ለአጐታቸው ልጅ ሸውጋ ጊዮርጊስ አጠገብ ላለው እኔ ጢት ሚያዝያ ፳፫ ቀን እመጣለሁ ብለው በሬውን በዋዜማው እንዲያርዱላቸው አስረክበው ኼዱ ያም አደራ የተረከበው ሰው የሚያዝያ ጊዮርጊስ ዋዜማ ወስዶ ማረድ ሲገባው ሞኝ ስለነበረ አንድ ወር አርሼ ማሽላ ዘርቼ በት ለግንቦት ጊዮርጊስ አርደዋለሁ ብሎ አስቦ ሳለ ሚያዝያ ፳፬ ቀን ጢት ከበሬው ቢኼድ በሬው ሞቶ አገኘው ወዲያው ተሸክሞ ሥጋውን ቢሄድ ንቡ ዘሪያውን ከቦ አላስገባም አለው የአደረገውን ሁሉ ኃጢአቱን ከተናዘዘ በኋላ ነፍስ ያለው የራሱን የቀንበር በሬ ይዞ ሲመጣ በሬውም ስተት ብሎ ከቅኔ ማኅሌቱ ገብቶ ፊት ለፊት ከአለው ከቅዱስ ጊዮርጊስ ሥዕል ፊት ቆሞ ሦስት ጊዜ ጮኸ በዚህም ጊዜ ታቦቱ ሲወጣ በሬውም አብሮ ከታቦቱ ጋር ያለ አንዳች ነጂ ከዞረ በኋላ ደጀ ሰላሙ በር ላይ ኼዶ ተኝቶ በሞት ተሰናበተ ይህ ነው አሳ ጐርጓሪ ዘንዶ አወጣ የሰው ፈላጊ የራሱን አጣ ማለት ሰው እንዴት እምነቱን ያጠፋል እንዴት አደራውን ይበላል ይህ ነው ታቦት ማለት የሰው ልጅ ከዚህ ሌላ ተአምር አለ ? ይህንን ያደርጋል ቅዱስ ጊዮርጊስ ተሳዩም ከሐዲውም አሁን በሕይወት አሉ ። ታሪኩን ይናገራሉ ይህም የተደረገው ሚያዚያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ነው የበለዓምን አኸያ ያናገረ አምላክ ዛሬም በበሬ ላይ አድሮ ተአምሩን ሠራ ፫ኛው ተአምር ደግሞ አቶ ካሴ በላይ የተባሉት ሰው ልጃቸውን ድረው ሳሉ በማንኛውም ሰው ሲዳር ሚዜዎቹ እየዞሩ በሚጫወቱበት ጊዜ በቅዱስ ጊዮርጊስም ቤተ ክርስቲያን ከበሩ ላይ ቁመው ይዘፉኑ ስለነበረ እነዚህም ከላይ ስማቸው የጠቀስነው ለጊዮርጊስ ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ካህናቱ ሊቃውንቱም ዋዜማ ቁመው ዘጠኙም ሚዜዎች ተሳልመው ሲወጡ ከሙሐሩ ላይ አምስት ብር በጨርቅ ተጠቅልሎ የተቀመጠውን ብር አንደኛው ሚዜ በማንሣት ደብቆ ይዞ ሲወጣ ወዲያውኑ ከግቢው ሳይወጣ ዓይኑ ጠፋ ይባስም ብሎ ንቦች ከበቡት ጓደኞቹም ተደናግጠው ሮጠው ኼደው ለካህናቱ ነገሩ ካህናቱም ተሰብስበው መጥተው ቢጠይቁት ከሙሐሩ ላይ የተቀመጠውን አምስት ብር እንደያዘና እንደሰረቀ ነገራቸው እየመሩም ወስደው ከአነሣበት ቦታ እንዲያስቀምጠው ካደረጉ በኋላ ጓደኞቹ እየመሩ ወደ ቤቱ ወስደው ጣሉት እርሱም ለሦስት ቀናት ያህል ዓይኑ ጠፍቶ የሙሽራውን ደስታ ሳያይ በዓልጋ ላይ ተኝቶ ከቆየ በኋላ በአራተኛው ቀን ወደ ጊዮርጊስ ቤተ መቅደስ

(ወደ ገጽ ፺ ዞሯል)



# ዜና ዕረፍት

የሊቀ ዲያቆናት ኪሮስ ገ/ሥላሴ አጭር የሕይወት ታሪክ ፡ ሊቀ ዲያቆናት ኪሮስ ገ/ሥላሴ ከአባቱ ቄስ ገ/ሥላሴ ሐጐስና ከእናቱ ከወ/ሮ ወለተ ኪዳን ገ/እግዚአብሔር በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም በትግራይ ክ/ሃገር በተንቤን አውራጃ እንዳ ኢየሱስ በተባለ ቦታ ተወለደ ። ከዚያም ዕድሜው ለትምህርት እንደደረሰ በዚሁ በተወለደበት በተንቤን አውራጃ በእንዳ ኢየሱስ ገዳም ለዲቁና የሚያበቃውን መንፈሳዊ ትምህርት አጠናቆ የዲቁና ማዕረጉን ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከተቀበለበት ዕለት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግል ኖሯል ።

ሊቀ ዲያቆናት ኪሮስ ገ/ሥላሴ በነበረው የመንፈሳዊ ትምህርት ፍላጎት በጐንደር ክ/ሀገር በደባርቅ አውራጃ ከመምህር ጐሐጽባህ ቅኔን ከነአገባቡ የተማረ ሲሆን አዲስ አበባ አባቱ ከሚያገለግሉበት ወደ መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን እንደመጣ በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ቅዳሴና ሐዲሳትን ከመምህር መንግሥቱና ከብፁዕ አቡነ እንድርያስ ዘንድ ተምሯል ።

ሊቀ ዲያቆናት ኪሮስ ገ/ሥላሴ በዘመናዊ ትምህርቱ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል በሀሐይሎ ሥራ ት/ቤት ካጠናቀቀ በኋላ ከ፯ኛ እስከ ፲፪ኛ ክፍል ያለውን ትምህርት በዳ ምኒልክ ት/ቤት ከማጠናቀቁም በላይ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በካቴድራል ት/ቤት በፈረንሣይኛ በዐረብኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ዲፕሎማ ተቀብሏል ። በአሁኑ ጊዜም በማታው ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዓመት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ትምህርቱን በመከታተል ላይ ይገኝ ነበር ።

ሊቀ ዲያቆናት ኪሮስ በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ከ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዲቁና በሊቀ ዲቁና ሥራ ተመድቦ በትሕትናና በታዛዥነት በትጋት እና በታማኝነት በማገልገል ላይ እንደነበረ አዳም ሆይ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ በተባለው አምላካዊ



ሊ.ዲ. ኪሮስ ገ/ሥላሴ ይህ ነበር ።

ትእዛዝ መሠረት ምንም ሕመም ሳያገኘው ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ከሌሊቱ በ፱ ሰዓት በተወለደ በ፳፭ ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል ።

ሊቀ ዲያቆናት ኪሮስ ገ/ሥላሴ በዕድሜው ገና ልጅ ሆኖ የሚሠራው በጎ ሥራ ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊና በዕውቀት የጐለመሱት አባቶች ከሚሠሩት በላይ መሆኑን በታዛዥነቱና በቀና አስተሳሰቡ ያስመሰከረ ወጣት ነበረ ፡ ሊቀ ዲያቆናት ኪሮስ ገ/ሥላሴ በሞት እስከተለየን ድረስ በሕይወቱ ሳለ እንኳን አባቶቹን ቀርቶ መሰል እኩዮቹን የማያስቀይም የልጅ አዋቂ ነበር ሊቀ ዲያቆናት ኪሮስ ገ/ሥላሴ እጅግ ተወዳጅና ሁሉን አፍቃሪ በመሆኑ እግዚአብሔር ያስተማጠውን ዕቃ መውሰድ ስለሚችል ጠርቶታል ስለዚህ ተወዳጁ ልጅ በሥጋው ከሚወዱትና ከሚወዳቸው አባቱ ዘመዶቹና ወንድሞቹ ቢለይም እስከ አሁን በአጭር ዕድሜው ያተረፈው መልካም ስም ለታሪክ የሚተላለፍ መሆኑን ስናሳብ እናንተ የአባቱ ብሩካን ወደኔ ኑ ተብለው ከሚጠሩት ጻድቃን መካከል ነፍሱን እግዚአብሔር እንዲያኖርልን በጸሎት በመማፀን ለቤተሰቦቹ ለወላጆቹ ለዘመዶቹና ለጓደኞቹ እግዚአብሔር ብርታትና መጽናናትን ይስጣችሁ እንላለን ።

ከመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ሰበካ ጉባኤ



www.ethiopianorthodox.org

# “የዓይን ማዝ” (ትራኮማ)

የዓይን ማዝ (ወይም በእንግሊዝኛ ትራኮማ) በመባል የታወቀው ተላላፊ የዓይን በሽታ ለብዙ ሰዎች በዓይን ሕመም መሰቃየትና መታወር ዓይነተኛ ምክንያት ነው። የትራኮማ በሽታ ከሌሎች የዓይን በሽታዎች ተለይቶ ከታወቀ ብዙ ዘመን ሆኖታል ጥንት በግብፅ በግሪክና በሮማ አገር በሽታው ተለይቶ ይታወቅና ሕክምናም ይደረግለት እንደነበር ታሪክ ይገልጻል ። አሁንም በሽታው በብዛት የሚገኘው በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በእስያ በሜድትራኒያን ባህር አካባቢ ባሉ አገሮች በአፍሪካና በደቡብ አሜሪካ ሲሆን በኢትዮጲያም ውስጥ ይህ በሽታ ብዙ ሰዎችን እንደሚያሰቃይ ታውቋል ።

የዓይን ማዝ በሽታ በብዛት የሚያጠቃው የግል ንጽሕና የሚጎድላቸውን ሰዎች ሲሆን የአካባቢው ንጽሕና ባልተጠበቀ መንደር ተፋፍጎና ተጨናንቆ መኖር ለዚህ በሽታ መዛመት አመቺ መሆኑ በጥናት ተደርሶበታል ። በቤተሰብ ውስጥ አንድ ሰው በዓይን ማዝ ከተለከፈ በሽታው ወደ ሌላ በቀላሉ ሊዛመት ይችላል ።

ይህንን በሽታ የሚያመጡት እጅግ ረቂቅ የሆኑ ቫይረስ የሚባሉ ተሕዋስያን ናቸው እነዚህ ቫይረሶች ከሕመምተኛው ሰው ወደ ጤነኛው ሰው በብዙ ዓይነት መንገድ ይተላለፋሉ በጤነኛው ውስጥ ከገቡ በመራባት በሽታውን ቀስ በቀስ ይጀምራል ።

<u>በሽታው ከአንዱ ወደ ሌላው እንዴት ይተላለፋል?</u>

## ጤናችን

፩ኛ) በዚህ በሽታ የተለከፈ ሰው የታመሙ ዓይኖቹን በነካካበት ወይም ባሻሸበት እጁ የጤነኛ ሰው ዓይን የነካካ እንደሆን በሽታውን ለማስተላለፍ ይችላል እንዲሁም ደግሞ ጤነኛው ሰው የበሽተኛውን ዓይን ነካክቶ እጆቹን በሳሙናና በውኃ ሳይታጠብ የራሱን ዓይን ሲነካ በሽታውን ወደ ራሱ አስተላለፈ ማለት ነው ።

፪ኛ) ሕመምተኛው በተጠቀመበት ፎጣ መሐረብና በሌሎችም ዕቃዎች በመጠቀም በሽታው ከአንዱ ወደ ሌላው ለመተላለፍ ይችላል ።

፫ኛ) ዝንቦች ብዙ ዓይነት በሽታዎች እንደሚያስተላልፉ የታወቀ ነው ። የዓይን ማዝ በሽታካለበት ሰው ዓይን አካባቢ በማረፍ የበሽታውን ጀርሞች ተሸክመው ከጤነኛ ሰው ዓይን ላይ ሲያርፍ በሽታውን ወደዚህ ሰው ዓይን ለማስተላለፍ ይችላሉ ።

<u>በሽታው ሲይዝ የሚያሳያቸው ምልክቶች</u>

፩ኛ) በዓይን ውስጥ የመለብለብና የመቆጥቆጥ ስሜት ያመጣል። ይህንን የአካልና የሞራል የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቅ ዓይነ ስውርነትን ለመከላከል የብሔራዊ ዓይነ ስውርነት መከላከያ ፕሮጀክት ተቋቁሟል ። ብዙ አስተዋጽኦም በማድረግ ላይ ይገኛል ። በአደረገው ክትትል በሀገራችን ፩.፭% ዓይነ ሥውራን መኖራቸው ከጥቂት ዓመታት በፊት ተደርሶበታል ። ዓይነ ስውርነት ሊያስከትሉ የሚችሉ በሽታዎች ፩. ዓይነ ማዝ ፡ የሞራ ግርዶሽ ሕፃናትን የሚያጠቁ ልዩ ልዩ በሽታዎችና ኩፍኝ የቪታሚን ኤ ማነስን ይጨምራል ።

የዓይን የውስጥ ግርዶሽና የደም ግፊት መጨመር ዋነኞች ናቸው ። በቅርብ ጊዜ ከምድረ ገጽ የጠፋው ፈንጣጣም ለብዙ ሺህ ሰዎች የዓይን ብርሃን ማጣት ምክንያት ሲሆን ቆይቷል ይህ ድርጅት ሥራውን በሚገባ እያከናወነ በመገኘት በክፍላተ ሀገራትም ቅስቀሳ በመድረግ ከላይ የጠቀስኩት 1·5% የነበረው የዓይነ ስውርነት ቁጥር በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ፺፪፻ ሺህ ዕውራን መኖራቸውን መዝግቧል ። ዓይነ ስውርነት በግለሰብ ላይ የሚያደርሰው የዓይን ብርሃን ማጣትና የኑሮ መቃወስ ብቻ ሳይሆን በሀገር ደረጃም ከፍተኛ የሶሻልና የኢኮኖሚ ችግር የሚያደርስ ነው ለምሳሌ ያህል በኢትዮጵያ አሉ ተብለው የሚገመቱትን ፺፪፻ሺ ዓይነ ሥውራንና እነርሱን የሚመሩትን ከአምራችነት የሚፈናቀሉትን ጤናማ ግለሰቦችን መንከባከብ የሚያስከትለውን ወጭ መገመት ይበቃል ። በዓለም ላይም ከ፴ ፴ ሚሊዮን የሚሆኑ ዓይነ ስውራን ይገኛሉ ከነዚህ ውስጥ ሶስት አራተኛው እጅ የሚገኙት በታዳጊ አገሮች ውስጥ ነው ።

ስለዚህ የድርጅቱ ዓላማ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓላማ መሆኑን በመረዳት የሰበካ ጉባኤ ጽ ቤቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ በየአብያተ ክርስቲያናቱ አካባቢ በየኔቢጤነት ገንዘብ ለማግኘት ሲባል ሕፃናትን መለመኛ እንዳያደርጉ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

መልአከ ሕይወት ይትባረክ
ዓለሙ



www.ethiopianorthodox.org

# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፣

የስልክ ቁ·
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፣